# የባላንጣው ዘር

ዛሬ ማታ ጌታ ቢፈቅድ፡ ቁም ነገሩን እንዲሰጠን፡ አጠር ያለች ጽሑፍ፡ ወይም አጠር ያለች ምንባብ፡ ከቅዱስ ማቴዎስ 13:24 እስከ 30። በመቀጠል በጥቂት ደቂቃዎች—ከ 36 እስከ 40፡ ማንበብ እፈልጋለሁ። አሁን ከቅዱስ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ 13፡ ከቅዱስ ማቴዎስ 13ኛው ምዕራፍ ከቁጥር 24 ይጀምራል። ቃሉ ሲነበብ በደንብ አድምጡት። የእኔ ቃል ያልፋል፡ የእርሱ ግን አያልፍምና።

**ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው፡ እንዲህም አለ፡ መንግሥተ ሰማያት በእርሻው መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመሰላለች፤**

**ሰዎቹ ሲተኙ ግን፡ ጠላቱ** መጣና **በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ፡ ሄደ።**

ስንዴውም **በበቀለና፡ በአፈራ ጊዜ፡ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ።**

**የባለቤቱም ባሮች ቀርበው፡ ጌታ ሆይ፡ መልካምን ዘር በእርሻህ** ዘርተህ **አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ አሉት?**

እርሱም **ጠላት ይህን አደረገ፡ አላቸው።** ባሮቹም **አሉት፡ እንግዲህ ሄደን... ብንለቅመው ትወዳለህን?**

**እርሱ ግን፡ እንክርዳዱን ስትለቅሙ፡ ስንዴውን ከእርሱ ጋር** እንዳትነቅሉት፡ **አይሆንም አላቸው።**

ተዉአቸው **እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆችን** እልካለሁ፡ **እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ፡ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፡ ስንዴውን ግን** በጎተራዬ **ክተቱ እላለሁ አለ።**

2 “እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙና፡ በየነዶው እሰሩ፡” የሚለውን አስተውላችሁታል? ትላንትና ማታ፡ በጸሎት፡ በካታሊና ተራሮች ራስ ላይ ቁጭ ብዬ ሳለሁ ቃሉን እያነበብኩ በነበርኩበት ጊዜ፡ ለዛሬ ጉባኤ የሚሆነን እንግዳ ነገር መጣልኝ። “ዛሬ ማታ ለመናገር ስለምፈልገው ነገር ቃል ከወዴት ልሰብስብ? ” ብዬ አሰብኩ፤

3 እኔም ወርጄ **ባላንጣ** የሚለውን ቃል አገኘሁ፡ መዝገበ ቃላቱን ከፍቼ **ባላንጣ** ምን ማለት እንደሆነ ተመለከትኩ። እንደ ዌብስተር አባባል፡ ትርጓሜው “አለመግባባትን የሚዘራ፡” ወይም—ወይም፡ “ተቃራኒ መሆን” ይለዋል፡ “አለመግባባት፣ የመለያየትን ነገር የሚዘራ፡” ወይም፡ “ቀድሞ ከነበረው ነገር የሚጻረር።” ስለዚህ የዛሬ ማታ ርዕስ፡ **የባላንጣው ዘው፡** ብዬ እንድሰይመው ተሰማኝ። እኛ ወደ እሱ ስንቀርብ ጌታ ቃሉን እንደሚባርክ እመኑ።

4 በቁጥር 36 እና—እስከ 43 ድረስ፡ ይህ ዘር እንዴት እንዳደገ፡ እንዴት እንደተረጎመው እናውቀዋለን። በዚያ ላይ እያለን፡ ያንን ደግሞ እናንብበው፡ ከቁጥር 36 እስከ 43።

> በዚያን ጊዜ **ሕዝቡን** ከሸኛቸው **በኋላ፡ ወደ ቤት** ገባ፤ **ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፡ የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጕምልን፡ አሉት።**
>
> እርሱም **መልሶ እንዲህ አላቸው፡ መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤**
>
> እርሻውም **ዓለም ነው፤ መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፤**
>
> የዘራውም **ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፤ አጫጆችም መላእክት ናቸው።**
>
> **እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፤ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል።**
>
> **የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፡ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ፡ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፤**
>
> **ወደ እቶን እሳትም፡ ወደ** እሳት **ይጥሉአቸዋል፡** በዚያም **ልቅሶ ይሆናል፡** ወይም ዋይታና **ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።**
>
> **በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው... ይሰማ።**

5 ይህ ኢየሱስ ራሱ፡ የምሳሌውን ትርጓሜ ሲሰጥ ነው፡ ስለዚህ ትርጓሜው ምን ማለት እንደሆነ እውቀናል። እና አሁን ወደዚህ፡ ስለዚህ የዘር መዝራት፡ እና—የመኸር አጨዳውን በተመለከተ፡ ኢየሱስ ትርጉሙን ሰጥቶናል። ይህም ኢየሱስ ይህን ምሳሌ የተናገረው በእርሱ ዘመን እንደሆነ አምናለሁ፡ የተናገረው ግን ለዓለም ፍጻሜ፡ ማለትም፡ ለዘመን ፍጻሜ፡ **ለዚህ** ጊዜ ነበረ። ዛሬ ማታ ይህ ትንሽ ፅሁፍ አሁን እኛ ለምንኖርበት ወቅት እጅግ የሚመጥን ነው ብዬ አምናለው፡ ምክንያቱም ኢየሱስ በግልጽ እዚህ ላይ "መኸሩ በዚህ ዓለም መጨረሻ ላይ ይሆናል" በማለት ተናግሯል፡ መጨረሻው ሲደርስ፡ ሰንዴውን ወደ መሰብሰብ እንክርዳዱን ደግሞ ለቅሞ ወደ ማቃጠል ይሆናል፡ ሰንዴውም ወደ መንግሥቱ ይሰበሰባል። በዚህ መንገድ እንደሚሆን አምናለሁ።

6 ሌላም በዚህ መንገድ እንዳምን ያደረገኝ ቃል፡ እዚህ ጽፌዋለሁ፡ ማቴዎስ 24:24 ላይ፡ ስለ ዘሩ—ስለ ባላንጣው ዘር—የሚናገርበት፡ ሰፍራ ነው። ኢየሱስም የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡት እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ሁለቱም እጅግ የተቀራረቡ ይሆናሉ ብሏል። ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ይሆናሉ።

7 በሌላ ቦታም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ዝናብ በጻድቃን እና በኃጢአተኞች ላይ ይዘንባል ተብሎ ተጽፏል።

8 በጴንጤቆስጤ ሰዎች መካከል ለመጀመሪያ የተገኘሁ ጊዜ እስታውሳለሁ። ሚሻዋካ፣ ኢንዲያና ነበር። ሰሜን እና ደቡብ በአንድነት በተሰበሰቡበት፡ ታላቅ የአውራጃ ሰብሰባ ላይ፡ እንደዚህ ባለው አዳራሽ ውስጥ ነበርኩ። በዚያ ዘመን በነበረ መለያየት፡ ምክንያት፡ እዚያ መገናኘት ነበረባቸው። በጴንጤቆስጤ

ወንድሞች መካከል ሁለት ታላላቅ መደቦች ነበሩና። ስለነሱ ስሞቼ አላውቅም ወይም አግኝቻቸው አላውቅም ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ በልሳኖች ሲናገሩ ሰማሁ። ሰብሰባው ላይ፡ ከእነርሱ እንዱ ሰላልነበርኩ... ወጣት የባፕቲስት አገልጋይ ነበርኩና፡ በጉባኤው፡ ከኋላ ላይ ቁጭ ብዬ ነበርኩ። እና ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዎች በልሳኖች ሲናገሩ በሰማሁ ጊዜ፡ አስታውሳለሁ ምን እንደሆነ—ስለ ምን እንደነበር እንኳ፡ አላውቅም ነበር። ከዚያ ሁለት ሰዎች፡ በዋነኝነት፡ ከፊት ለፊት ተቀምጠው ነበር፡ አንደኛው በልሳን ሲናገር ሁለተኛው የተናገረውን ይተረጉመዋል። እና፡ ወድያው፡ መጽሐፍ ቅዱሴን የቻልኩትን ያህል ማጥናት ጀመርኩ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነም ተረዳሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ፣ የመንፈስ ቅዱስም ስራ ነው።

9 እና፡ ከአንድ ቀን በኋላ... በዚያ ምሽት ልቤ በጣም ተነሳሳ። በቆሎ ሰብል ውሰጥ ተኛቼ አደርኩ። አ—አልጋ የምከፍልበት—በቂ ገንዘብ አልነበረኝም፡ ወደ ቤቴ የሚያደርሰኝ ብቻ ነበረኝ፡ ሁለት ቀናት ያለፋበት፡ ጥቂት ዶናት፡ ወይም ሮል ይዤ ነበር፡ ያም ደግሞ፡ ለቁርሴ ነበር። አብሬአቸው መመገብ እችል ነበር፡ ይሁን እንጂ ገንዘብ ማዋጣት አልችልም። እነዚያ፡ የ1933 ቀናት፡ አስቸጋሪ ጊዜ ሰለ ነበሩ፡ በጣም ከባድ—ሁኔታ ነበር። እና እንዲህ አሰብኩ፡ “እንደው፡ አብሬአቸው መብላት... አልፈልግም፡ እሰቲ የያዙትን ግን ልይ። ለእኔ የሌለኝ ነገር ይዘው ነበርና።”

10 ስለዚ በዛ ማለዳ... ጥሪ ተደረገልኝ፡ “አገልጋዮች የሆናችሁ ወደ መድረኩ እየመጣችሁ ማንነታችሁ፡ እና ከየት እንደመጣችሁ፡ ራሳችሁን አስተዋውቁ” ተባለ።

11 መልካም፡ እ—እኔ፡ “ወንጌላዊ፡ ዊልያም ብራንሀም፡ ከጀፈርሰንቪል፡” ብዬ ቁጭ አልኩኝ። በመድረኩ ከነበሩት አገልጋዮቹ ሁሉ በእድሜ ትንሹ እኔ ነበርኩኝ። በነጋታውም በመድረኩ ንግግር እንዳደርግ ጋበዙኝ። ከተናገርኩ በኋላ፡ በጣም፡ ልዩ የሆነ ጊዜ ሰለነበረን፡ ብዙ ሰዎች ተዋወቅኩኝ ወደ ቤት ክርስትያናቸው እንድመጣ ይጋብዙኝ ነበር። በኋላ...

12 ከዚያ በኋላ፡ እንዲህ፡ አሰብኩ፡ “ልሳን ሲናገር እና ሲተረጉም ያየኋቸው ሁለት ሰዎችን ባገኘኋቸው ብየ አሰብኩኝ!” በልቤ ሲቀጣጠል የነበረው እሱ ነውና፡ በጣም ፈለግኳቸው። እንደው፡ አሰቀድሜ እንደነገርኳችሁ፡ የምትጎትቷት ትንሿ ሰጦታ። ሰጦታዎች እና ጥሪዎች ያለ ንሰሃ እንደሚሰጡ፡ በህይወታችሁ አብረው የሚቆዩ መሆናቸውን፡ ታውቁታላችሁ። እያችሁ፡ የእግዚአብሔር ሰጦታዎች ሲሆኑ፡ ከእናንተ ጋር አብረው የሚወለዱ ናቸው። ሰለዚህ በእኔም ሁል ጊዜ፡ ከልጅነቴ ጀምሮ፡ ሁል ጊዜ በእኔ ላይ ይታይ ነበር፡ ሕይወቴን የሚያውቁት ሰዎች፡ ያ እውነት እንደሆነ ያውቃሉ። እንግዲህ፡ አሁን ሳሰበው... ራዕይ ብለን የምንጠራው ነገር፡ ያኔ ምን እንደነበረ አላውቀውም፡ በፍጹም አላውቀውም ነበር። እኔ ግን እንደው፡ “ሰዎቹን ባነጋገርኳቸው ብዬ አሰብኩ!” እንዲሁም፡ በህንጻው ውሰጥ የነበረው መንፈስ እውነተኛ የእግዚአብሔር መንፈስ ይመስል ነበርና።

13 ስለዚህ ከሁለቱ አንደኛውን—አነጋገርኩትና፡ ጥቂት ጥያቄዎችን ጠየቅኩት፡ እውነተኛና ቅን ክርሰቲያን ሆኖ አገኘሁት። ሰውዬው እውነተኛ አማኝ ሰለመሆኑ፡ ጥርጥር የለውም። ሁለተኛው ሰው፡ ባናገርኩት ጊዜ ግን፡

በህይወቴ ከገጠሙኝ ግብዝ ሰዎች፡ አንዱ እሱ ነው። ሰውዬው... ሚስቱ ወርቃማ-ጸጉር ያላት ሴት ስትሆን፡ ጥቁር-ጸጉር ካላት ሌላ ሴት... ሁለት ልጆች ወልዷል። እኔም፡ “ታድያ፡ ይህ ምንድነው አልኩኝ? በቃ፡ እንደው—— ተቀላቀለብኝ። ነገሮች ከቃሉ ይሁኑ፡ ካልሆኑ ግን ልክ አይደሉም፡ የሚል ወግ አጥባቂ ነኝ። እነሆም መንፈሱ ሲገለጥ፡ እኔ እንደማውቀው፡ በሚገባኝ እውነት፡ ትክክለኛ ሰው ሲሆን፡ ሌላኛው ግን ፈጽሞ መልካም ያልሆነ ነበር፤ መንፈስ ግን በሁለቱም ይወርድ ነበር። አሁን፡ ያ እንዴት ሊሆን ቻለ? ” በቃ፡ እንቆቅልሽ ሆነብኝ።

14 ከሁለት ዓመት በኋላ፡ ለመጸለይ በምሄድበት ዋሻ ውስጥ እየጸለይኩ ነበር። በዋሻው ውስጥ አቧራ ለብሻለሁ፡ እና አንድ ቀን ከሰአት በኋላ ወጣሁ፡ መጽሐፍ ቅዱሴን ግንድ ላይ አስቀመጥኩት፡ ነፋሱም ሲነፍስበት፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 6 ከፈተ። በመጨረሻው ዘመን ከእውነት ብንወድቅ እንዴት እንደምንሆን፡ የሚናገረውን ክፍል ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት እንደማይኖር፣ ዳግመኛም ለንስሐ ራሳችንን ማደስ፣ ለመረገጥ የቀረበ፡ ፍጻሜውም ለመቃጠል የሆነ፡ እሾህና አሜከላ ቢያበቅል፣ ዝናብ ግን፡ ብዙ ጊዜ ምድርን ሊያጠጣ፡ እና ሊያበቅል ይመጣልና፣ እሾህና አሜከላው ካበቀለ ግን ይጣላሉ፡ ሰንዴው ይሰበሰባል። እኔም “አይ፡ ነፋሱ በአጋጣሚ ከፍቶት ነው፡” ብዬ አሰብኩ። እንደው፡ መጽሀፍ ቅዱሰን እንደገና ዘግቼ አስቀመጥኩት። እስኪ አሁን ደግሞ፡ “እንደው፡ እንዲህ ላድርግ ሰል... ” ንፋሱም መጥቶ እንደገና ከፈተው። ያ ሦስት ጊዜ ሆነ። እና “እንግዲህ፡ ይሄ፡ እንግዳ ነገር ነው፡” ብዬ አሰብሁ።

15 ከዛም ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና፡ ማሰብ ጀመርኩ፦ “ጌታ ሆይ፡ ይህን መጽሐፍ እንዳነበው፡ በተለይ... ደግሞ፡ ‘ለመጣል የቀረበ፡ ፍጻሜው የሚቃጠል እሾህ እና አሚኬላ’ የሚለው ላይ በደረሰኩ ጊዜ፡ ለምን ገለጥክልኝ አልኩት? ” ወዲያ ማዶ እየተመለከትኩ፡ “ይሄን፡ ለምን ከፈትክልኝ? ” ብዬ ማሰብ ጀመርኩ...

16 እንግዲህ፡ እውነተኛ ራዕይ ከሆነ ያለ አንዳች ጉተታ ይመጣል። እግዚአብሔር ነው። አያችሁ? እነሆ አየሁ ምድር ከፊት ለፊቴ ዞራ አየኋት፡ በደንብ ተዘጋጅታም ነበረች። እነሆም ነጭ የለበሰ ሰው፡ ሰንዴ ዘርቶ ሲሄድ አየሁት። እሱ ዘርቶ አድማስ በተሻገረ ጊዜ፡ እነሆ ሌላ፡ የሚሰቀጥጥ ሰው መጣ፡ ጥቁር ለብሶ ነበር፡ በሰፍራውም ሁሉ እንክርዳድ ይበትን ነበር። አብረውም በቀሉ። በበቀሉም ጊዜ፡ ዝናብ ያስፈልጋቸው ስለነበረ፡ አብረው ተጠሙ። ሁሉንም ትንንሽየ ራሶቻቸውን አጎንብሰው “ጌታ ሆይ፡ ዝናቡን ላክልን፣ ዝናቡን ላከው፡” ብለው መጸለይ ጀመሩ። እነሆም ታላቅ ደመና መጣ፡ ዝናብም በሁለቱም ላይ ዘነበ። ዝናብም በዘነበ ጊዜ፡ እነሆ ትንንሾቹ ሰንዴዎች በደስታ “ጌታ ይመስገን! ጌታ ይመስገን!” እያሉ ዘለሉ፤ ትንንሾቹ እንክርዳድም ጎን ለጎን እየዘለሉ፡ “ጌታ ይመስገን! ጌታ ይመስገን!” ይሉ ነበር፤

17 ከዚያም ራእዩ ሲተረጎም፡ ዝናብ በጻዲቁ እና በሐጢአተኛው ላይ ይዘንባል ሆነ። በጉባኤ ላይ በሚወርደው፡ በአንዱ መንፈስ፡ ግብዞቹም፣ ክርስትያኖቹም፣ ሌሎችም አብረው ይደሰቱበታል። በትክክል እንደዛ ነው። እሺ ምን ማለት ነው? በፍሬአቸው ይለያሉ። አያችሁ? የምትለዩበት ብቸኛው መንገድ ፍሬ ነው።

18 አሁን ይሄን እዩት፡ የበረሃ አጃ፣ ወይም የበረሃ ስንዴ እና ስብል አንዳንዴ ትክክለኛውን፡ የቤት ስብል ለመምሰል ያታልላል፡ የተመረጡትን እስከሚመስል ለማታለል የቀረበ ነው። እኔ እነዚህ ነገሮች መነገር እና መሰበክ ባለበት ዘመን፡ እየኖርን እንገኛለን ብዬ አስባለሁ።

19 በቁጥር 41 ላይ እናስተውል፡ በጣም ይቀራረባሉ፡ በዘመን ፍጻሜ ለይቶ ለማውጣት እስከማይችል ድረስ... እነሱን ለማለያየት የሚተማመንባት ቤተ ክርስትያን ልትኖር አትችልም፡ ለመለየት በሜቶዲስት ወይም በባፕቲስት፣ ወይም ጴንጤቆስጤዎች፡ በሉት አይሆንም። "እነዚህን ለመለየት መላእክቶቹን እልካቸዋለሁ፡" ብሏል። ክፉዎቹን እና መልካሞቹን የመለየቱን ስራ፡ የሚሰራ መልአክ እየመጣ ነው። ይህንንም ከእግዚአብሔር መልአክ በቀር ማንም ሊሰራው አይችልም። የትኛው ትክክል እና ስህተት እንደሆነ የሚናገር እሱ ነው። እግዚአብሔር በመጨረሻው ጊዜ መላእክቱን እንደሚልክ ተናግሯል። አሁኑኑ **እዚሁ** ይልካቸዋል ሳይሆን፡ በመጨረሻው ቀናት፡ መላእክቱን ይልካቸዋል ሁሉንም ይሰበስባሉ። ይህ የሚመጣው ጊዜ የመኸር ጊዜ መሆኑን እናውቃለን። **መልአክ** ሲተረጎም "መልእክተኛ" ማለት ነው። አሁንም... ማለት፡ በቤተክርስያን ዘመናት ውስጥ፡ ለሰባቱ አብያተ ክርስትያናት የተላኩ ሰባት መላእክት እንዳሉ እናውቃለን።

20 ዘሪዎቹ እና ዘር እነማን መሆናቸውን ሲናገር ስለ ማን እንደተናገረ አስተውሉ። አንደኛው፡ ዘር እየዘራ የወጣ ዘሪ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ጠላት ዲያብሎስም፡ ከኋላው መጥቶ፡ የባላንጣ ዘር ዘራ፡ በተዘራው ትክክለኛ ዘር ላይ ሌላ ዘር ተዘርቷል። ወዳጆች ሆይ፡ ዓለም ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ፡ በእያንዳንዱ ዘመን ላይ ይህ ሆኗል። በትክክል። ከመጀመሪያው ጀምሮ፡ ይህ ተመሳሳይ ነገር ነበረ።

21 አሁን እንግዲህ "የእግዚአብሔር ዘር፡ የእግዚአብሔር ቃል፡" ብሎአል። ኢየሱስ በአንድ ሰፍራ "ቃል ዘር ነው፡" በማለት ተናግሯል። እያንዳንዱ ዘርም እንደየ ዓይነቱ ፍሬ ያፈራል። አሁንም ክርስትያኖች፡ የእግዚአብሔር ልጆች፡ የመንግሥቱ ልጆች የእግዚአብሔር ዘር መሆን ካለባቸው፡ እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው፡ በዘመናቸው ስለተሰጠ የተሰፋ ዘር፡ በሚኖሩበት ዘመን የሚገለጡ የእግዚአብሄር ቃል መሆናቸው ነው። እግዚአብሔር ከመጀመሪያ ቃሉን ሰጥቷል፡ እያንዳንዱ ዘመን የራሱ ዘር፣ የራሱ ጊዜ፣ የራሱ የተሰፋ ቃል አለው።

22 ኖህ በመጣ ጊዜ፡ ለዛ ዘመን፡ የእግዚአብሔር ዘር፡ እና የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ መጣ።

23 ሙሴ በመጣ ጊዜ፡ የኖህ መልእክት ይዞ መምጣት አይችልም፡ አይሰራምና፡ ምክንያቱም ለዚያ ዘመን የሚሆን የእግዚአብሔር ዘር ነበርና።

24 ክርስቶስ ሲመጣም በኖህ ወይም በሙሴ ዘመን መምጣት አይችልም ነበር፤ ድንግል የምትፀንሰበትና ወንድ ልጅ የምትወልድበት፡ እርሱም መሲሕ የሚሆንበት የራሱ ጊዜ ነበረው።

25 አሁንም፡ በሉተር ዘመን፣ በዌስሊ ዘመን (የሜቶዲስት ዘመን)፡ እና በጴንጤቆስጤ ዘመን፣ በዘመናት ሁሉ ኖረናል፡ እያንዳንዱ ዘመን የየራሳቸው ተስፋ ቃል ተሰጥቷል። የዘመኑ ተስፋ ቃል የሚገልጡ፡ የዚያ ዘመን ሰዎች፡

የዘመኑ ዘር እነርሱ ናቸው፡ ኢየሱስ እዚህ በተናገረው መሠረት፦ “የመንግሥቱ ልጆች ናቸው።” ትክክል ነው። የመንፈስ ቅዱስ አሰራር ሲገለጥ የሚሰራባቸው ልጆቹ በዛ ትውልድ ውስጥ የመንግስት ዘር እነርሱ ናቸው።

26 ተከታተሉ፡ እንክርዳዶች፡ ጠብ ዘሪው ጠላት፣ ማለት ሰይጣን፡ ወይም—ወይም የባላንጣው ዘር የዘራቸው ናቸው፡ ይህን ክፉ ድርጊት የፈጸመው ጥፋተኛ እሱ ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የሰው ልጆችን መከር፡ በምድር ላይ በዘራ ጊዜ ሰይጣን ከመጀመርያው ጀምሮ ዘሩን ዘርቷል። በርግጥ፡ አዳም፡ የ—እውቀት እውነት መኖሩ ገና ሳያውቅ፡ ክፋም ይሁን መልካም፡ ወደ ማወቅ ፈጽሞ ገና ሳይለይ።

27 ጋሻ ይሆናቸው ዘንድ፡ እግዚአብሔር ለልጆቹ ቃሉን እንደሰጣቸው ተረድተናል። ይህም... ከእግዚአብሔር ቃል በቀር ሌላ ጋሻ የለንም። ጋሻችን እርሱ ነው። ቦምቦች የለንም፣ መጠለያዎች የሉንም፣ ምንም መደበቂያ ቦታዎች የሉም፣ አሪዞና ወይም ካሊፎርኒያ፣ ማንም ይሁን አይሰራም፤ ያለን አንድ መከላከያ ብቻ ነው፡ እርሱም ቃሉ ነው። ቃልም ሥጋ ሆነ በመካከላችን አደረ፡ እርሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ብቸኛው መከላከያችን እርሱ ነው። በእርሱ ዘንድ ስንሆን፡ ደህና ነን።

28 ለእውነተኛው አማኝ ኃጢአት እንኳን አይቆጠርበትም። ይህን ታውቃላችሁ? ከእግዚአብሔር የተወለደ፡ ኃጢአትን አያደርግም፡ ኃጢአትንም ሊሠራ አይችልም። አያችሁ? አይቆጠርበትም። ለምን፡ ዳዊትም አለ፦ “እግዚአብሔር ኃጢአት የማይቆጥርበት ሰው ብጹዕ ነው።” በክርስቶስ ስትሆን፡ ኃጢአት የመሥራት ፍላጎት አይኖርህም። “መሰዋዕት አቅራቢው፡ አንዴ ከነጻ በኋላ፡ የኃጢአት ሕሊና አይኖረውም፡” አትመኙትምና። እንግዲህ፡ ለዓለም፡ ሐጢአተኞች ልትባሉ ትችላላችሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ግን፡ በክርስቶስ ስለሆናችሁ፡ እንዲህ አይደላችሁም። እግዚአብሔር የሚያየው አንተ ያለህበት እርሱን ብቻ ሲሆን፡ አንተም ኃጢአት በሌለው ሰው ውስጥ ስትሆን፣ ሐጢአተኛ እንዴት ትሆናለህ?

29 አሁን በዚህ የመኸር ወቅት። በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር ዘሩን በምድር ላይ ዘርቶ፡ በልጆቹ በቤተሰቡ ልብ ውስጥ ባደረገው ጊዜ፡ ይህም ቃሉን ይጠብቁ ዘንድ ነውና፡ ብቸኛው ጋሻቸው፡ ቃሉን መጠበቅ ነበር! እነሆ ጠላት መጥቶ ያንን አጥር ሰበረና፡ የእግዚአብሔርን ቃል የሚጻረር የባላንጣ ዘር ዘራ። ይህ ከመጀመሪያ ባላንጣ ከነበረ፡ አሁንም ነው። በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚጨመር ማንኛውም ነገር፡ አሁንም የባላንጣ ዘር ነው! ከማንም ይምጣ አያሳስበኝም፡ ቢፈልግ ከድርጅቶች፣ ቢፈልግ ከወታደራዊ ምንጭ፣ ቢፈልግም ከፖሊቲካዊ ሃይሎች ይምጣ፡ የእግዚኣብሄርን ቃል የሚቃረን ከሆነ፡ የባላንጣ ዘር ነው።

30 አንድ ሰው ቆሞ የወንጌል ሰባኪ ነኝ እያለ፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል” የሚል ከሆነ፡ ይህ የባላንጣ ዘር ነው። አንድ ሰው ቆሞ አገልጋይ ነኝ፣ የሆነ ቦታ የቤተ ክርስቲያን ፓስተር ነኝ ቢል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ (ከሥጋዊ አካሉ በስተቀር) በሁሉም ዝርዝር ውስጥ አንድ መሆኑን ካላመነ፡ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው መሆኑን ካላመነ፣ የባላንጣ ዘር ነው። “ተአምራትና ሐዋርያዊ ዘመን አልፏዋል” የሚል ከሆነ፡ የባላንጣ ዘር ነው። “መለኮታዊ

ፈውስ የሚባል ነገር የለም፡” ሲሉ፡ የባላንጣ ዘር ናቸው። ይህም ሁሉ በዓለም ሞልቷል። በዝቶም ሰንዴውን አንቋል።

31 የመጀመሪያው የባላንጣን ዘር የዘራው ዘሪ “ዲያብሎስ” የሚል ስያሜ እንደተሰጠው እናስተውላለን፡ ይህም በዘፍጥረት 1 ላይ፡ እንደነበረ እናውቃለን። አሁንም እዚህ ውስጥ፡ በማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 13 ላይ፡ እንዲህ እናገኛለን፡ አሁንም ኢየሱስ ቃሉን የሚቃረን ማንኛውንም ነገር “ዲያብሎስ” ይለዋል። እናም በዚህ በ1956፣ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በተቃራኒ፡ ባላንጣነትን የሚዘራ ማንኛውም ነገር፣ ወይም ማንኛውንም የግል ትርጓሜ የሚሰጥ ማንም ይሁን፡ የባላንጣ ዘር ነው። እግዚአብሔር አያከብረውም። በፍጹም። አይቀላቀልም። በርግጥ አይቀላቀልም። እንደ ሰናፍጭ ዘር ነው፤ ከማንም ጋር አይቀላቀልም፡ ልታዳቅሉት አትችሉም፡ እውነተኛው ነገር መሆን አለበት። የባላንጣው ዘር!

32 አሁን፡ እግዚአብሔር ዘሩን በኤደን ገነት በዘራ ጊዜ፡ አቤልን እንደ ወለደ ተረድተናል። ሰይጣን የባላንጣው ዘሩን በዘራ ጊዜም፡ ቃየንን ወለደ። አንዱ ጻድቅን ወለደ፡ አንዱ ዓመፀኛን ወለደ። ይህም ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን፡ የባላንጣን ቃል ስለሰማች፣ የኃጢአት ኳስ ያኔ በዚያ መንከባለል ጀመረ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየተንከባለለ ይገኛል። መላእክቶች መጥተው ነገሩን እስኪለያዩ ድረስ ሁሉንም አውጥተን አንችለውም፡ እግዚአብሔርም ልጆቹን ወደ መንግሥት ይወስዳል እንክርዳዱም ይቃጠላል። ሁለቱ የወይን አረጎች ተመልከቷቸው።

33 በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ጊዜ ቢኖረን መልካም ነበር፡ ይሁን እንጂ ዋና ዋና ቦታዎችን እንዳሰሳለን፡ ስለዚህ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ለታመሙ መጸለይ እንችላለን።

34 አስተውሉ፡ እዚህ ላይ ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው ዘሮቻቸው አብረው አደጉ በዛሬው ምሽት ፅሑፋችንም፣ በማቴዎስ፡ በምዕራፍ 13 “አብረው ይደጉ፡” ተባለላቸው። ስለዚህ፡ ቃየን ወደ ኖድ ምድር ሄደ፡ ለራሱን ሚስት አገኘ፡ እና አገባ፤ አቤልም ተገደለ፡ እግዚአብሔርም ሰፍራውን ይተካ ዘንድ ሴትን አስነሣው። ከዚያም የእውነት እና የስሕተት ትውልዶች፡ መንቀሳቀስ ጀመሩ። እንግዲህ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን፡ እነዚህ ሁሉ፡ መቀላቀል ጀመሩ፡ እግዚአብሄር… እግዚአብሄር እስኪያጠፋቸው ድረሰም ክፉዎች ሆኑ።

35 በመጨረሻ ግን ሁለቱ ዘሮች መጡ፡ የእግዚአብሔር ዘር እና የባላንጣው ዘር፡ መጡ ትክክለኛው ራሶቻቸውን ገለጡ፡ ሁለቱ በአስቆሮቱ በይሁዳና በኢየሱስ ክርስቶስ ተጠቃለሉ። እርሱም፡ የእግዚአብሔር ዘር ነበርና፡ እርሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነበር። የአስቆሮቱ ይሁዳም የጥፋት ልጅ ሆኖ ተወለደ፡ ከሲኦል መጥቶ ወደ ሲኦል ተመለሰ። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፡ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ነበር። የአስቆሮቱ ይሁዳ፡ በገዛ ባላንጣነቱ፡ የዲያብሎስ ዘር ነበር፡ ለማታለልም፡ ልክ እንደ መጀመሪያው፡ እንደ ቀድሞ አባቱ፡ እንደ ቃየን፡ ወደ ዓለም መጣ።

36 ይሁዳ የቤተክርስትያን አስመሳይ ብቻ ነበር እንጂ፡ ቅን አልነበረም። በእውነቱ እምነት አልነበረውም፡ ቢኖረው ኖሮ ኢየሱስን አሳልፎ አይሸጥም

ነበር። እርሱ፡ ግን፡ የባላንጣው ዘር ዘራ። ከዓለም ጋር፣ እና ከነዋይ ጋር፣ እንዲሁም ከኢየሱስ ጋር ጓደኝነት መመሥረት እንደሚችል አሰበ፡ ምንም ሳይጠቀምበት ግን ረፈደበት። የሞት ሽረት ሰዓት በመጣች ጊዜ፡ እርሱ ይህን ክፉ ነገር ባደረገ ጊዜ፡ ወደ ፊት በመሄድ እና ወደ ኋላ በመመለስ መካከል ያለውን መለያ መሰመር አለፈ። እንደ እታላይ ሆኖ፡ በሄደበት መንገድ መሄድ ነበረበት። የባላንጣው ዘር ዘርቶ፡ በዚያ ዘመን በነበሩ ታላላቅ ድርጅቶች ዘንድ፡ ከፈሪሳውያንና ከሶዶቃውያን፡ ሞገስ ለማግኘት ሞከረ። ለራሱም ጠቀም ያለ ገንዘብ ሰብስቦ፡ በህዝቡ መካከል አንጋፋ እሆናለሁ ብሎ አሰበ። ብዙ ሰዎች በሰው ፊት ሞገስ ለማግኘት ሲሞክሩ፡ በባላንጣው ይጠመዱ የለምን! በሰው ዘንድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ይሁንልን። ይሁዳ ግን እነዚህ ባላንጣነቶች በወረሱት ጊዜ ይህን አደረገ።

37 ኢየሱስም ቃል እንደ ሆነ እናውቃለን፡ ቅዱስ ዮሐንስ 1 ላይ፡ እንዲህ ይላል፦ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በመካከላችንም አደረ።" ስለዚህ፡ ቃል ዘር ነው፡ ዘሩም ሥጋ ሆነ በመካከላችንም አደረ።

38 ይሁዳም የጠላት እና የባላንጣው ዘር ከነበረ፡ እርሱም ሥጋ ሆኖ በአስቆሮቱ ይሁዳ ሰውነት በመካከላችን ዘንድ አደረ። እውነተኛ፡ እውነተኛው እምነት ኖሮት አያውቅም። እምነት ነው ብሎ **የሚያሰበው** ነገር ነበረው። ትክክለኛ እምነት አለ፡ እምነት የሚመስል-ማመንም አለ።

39 እውነተኛው የእግዚአብሔር እምነትም በእግዚአብሔር ያምናል፡ እግዚአብሔርም ቃል ነው፡ በእርሱም ሌላ አይጨመርበትም። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቃል ብንጨምር፡ ወይም አንድ ቃል ብናጎድል፡ ድርሻችን ከሕይወት መጽሐፍ እንደሚወሰድ ይነግረናል። በመጨረሻው የመዝጊያ ምዕራፍ፡ በራእይ 22፡18።

40 በመጀመርያ፡ መጀመርያ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አንዲት ቃል እንዳይተላለፉ፡ "እያንዳንዱ ቃል እንዲጠብቁ፡" በዚህ ቃል እንዲኖሩ ነገራቸው። ኢየሱስም፡ በመጽሐፉ ቅዱስ መካከል መጣና፡ በዘመኑ ተናገረ፡ እንዲህም አላቸው፦ "ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡ ከእግዚአብሔር አፍ—በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ።" በራዕይ ማገባደጃ ዘመንም፡ አስቀድሞ ተናገረን፡ እንዲህ አለ፦ "ከመጽሐፉ አንዲት ቃል የሚቀንስ፡ ወይም አንድ ቃል የሚጨምርበት፡ ዕጣ ፈንታው ከሕይወት መጽሐፍ ይወሰድበታል።"

41 ስለዚህ እውነተኛና፡ ያልተበረዘ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ፡ ብዥ የሚል ነገር ሊኖር አይችልም! በሰው ፈቃድ፡ ወይም እጅ በመጨባበጥ፡ ወይም በሆነ የጥምቀት ዓይነት ያልተወለዱ፡ የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች፣ የእግዚአብሔር ሴቶች ልጆች፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወልደው፡ ቃሉ የሚገለጥባቸው እነዚህ ናቸው። እውነተኛ የእግዚአብሔር ዘር ይህ ነውና!

42 ጠላት በሰርዓት ወይም በሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀላቅሎ ኦርቶዶክሳዊ ይመስላል። ይሁን እንጂ አይደለም... እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ማንኛውም ነገር፡ ባላንጣ ነው።

43 እንዴት እናውቃለን? "እሺ፡ እስኪ፡ የመተርጎም መብት አለህ ወይ?" እንላለን፡ ኖ፡ ስር! የእግዚአብሔርን ቃል የመተርጎም መብት ያለው ሰው የለም።

እሱ የራሱ ተርጓሚ ነውና። ራሱ ቃል ገብቶ፡ ራሱ ይፈጽመዋል፡ አተረጓጎሙም ይህ ነው። ቃል ይገባና፡ የገባው ቃል ይፈጽማል፡ ትርጓሜውም ይህ ነው። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጭ ማንኛውም ነገር ባላንጣ ነው! በትክክል!

44 አሁን፣ እንዳልኩት፡ ይሁዳ እውነተኛ እምነት አልነበረውም። አሰመሳይ-አማኝ ነበረ። የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ነው ብሎ ባሰበው በራሱ መንገድ—የራሱ እምነት ነበረው፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ነበረ ግን አላወቀውም ነበር። እንዲህ ባላደረገም ነበርና። በእግዚአብሔር ቃል እውነትነት ላይ የሚወላውል ሰው፡ የአሰመሳይ-አማኝ እምነት ያለው ነው። እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ በዚህ ቃል ላይ ይጸናል።

45 ከጥቂት ምሽቶች በፊት፡ እዚህ ከተማ፡ በአሪዞና ውስጥ ያለ ታላቅ፡ እና ታዋቂ ትምህርት ቤት ውስጥ፡ አገልጋይ የሆነ ሰው፣ ወደ እኔ መጥቶ፦ "ጊዜ ሲኖርህ፡" "አንድ ነገር ላይ ላርምህ—እፈልጋለሁ አለኝ።" (እኔም አልኩት... )

"እኔ የማውቀው ምርጥ ጊዜ ይህ ነው። ናና ቅረብ፡" አልኩት።

46 መጣና፡ እንዲህ አለኝ፦ "ሚስተር. ብራንሃም፡ በሙከራህ... ቅን እና ሐቀኛ ሰው እንደሆንክ አምናለሁ፡ ነገር ሐዋርያዊ አስተምህሮ ለዓለም ለማስተዋወቅ ትሞክራለህ።" "የሐዋርያት ዘመን'ኮ ከሐዋርያት ጋር አብቅቷል፡" አለኝ።

47 "ወንድሜ፡ በመጀመሪያ ልጠይቅህ የምፈልገው፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ በምሪት የተሰጠ እንደሆነ ታምናለህ፡" አልኩት?

"የስ፡ ሰር፡ በእርግጥ አምናለሁ፡" አለኝ።

48 ከዛ እንዲህ አልኩት፦ "እንግዲያውስ፡ የሐዋርያው ዘመን ያበቃበትን በቃሉ ውስጥ አሳየኝ? አሁን፡ የት እንዳለ አሳየኝና፡ አብሬህ አምናለሁ።" እንዲህም አልኩት፦ "ሐዋርያዊው ጸሐፊ፡ የመንግሥቱ ቁልፍ የነበረው ሰው፡ የሐዋርያት ዘመን በተጀመረበት በበዓለ ሃምሳ ቀን፡ 'ወንድሞች ሆይ፡ እንድንድን ዘንድ ምን እናድርግ?' ባሉት ጊዜ፡ እንዲህ አልቸው፦ 'ንስሓ ግቡ፡ ሐጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ሰጦታም ትቀበላላችሁ፡ የተሰፋው ቃል ለእናንተ እና ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና።' አሁንስ፡ ቃሉ እንዴት እርሰ በርስ ይቃወማል?"

ሰውየውም "ዛሬ ከባድ ጉንፋን ይዞኛል፡" አለ።

"እኔም እንዲሁ ይመስለኛል፡" አልኩት። አያችሁ?

49 እሰቲ ንገሩኝ፡ እግዚአብሔር እየጠራ ነውን? እግዚአብሔር አሁንም እየጠራ ከሆነ፡ እንግዲያውስ የሐዋርያት ዘመን አሁንም አለ። በእርግጠኝነት! ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው፣ ለጠራቸው፣ ገና ለሚጠሩ፣ ለሚጠራቸው ሁሉ ነውና፡ ኢየሱስ ክርሰቶስ ትናንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለምም፣ ያው ነውና አሁንም የሐዋሪያት ዘመን ይቀጥላል።

50 እንግዲህ፡ ይህ የባላንጣ ዘር በእያንዳንዱ ዘመን ዘር ሲዘራ ቆይቷል። በሚቀጥሉት አሰር ወይም አሰራ አምሰት ደቂቃዎች ውስጥ መጨረሰ የሚቻል ከሆነ፡ አደርገዋለሁ፡ ግን አይቻልም። በዘመናት ሁሉ ላይ... ሁላችንም፡ ብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስን እንብበናል። አሁንም ኢየሱስ ሲመጣ፡

ባላንጣውን ተጻራሪውን አገኘ። እርሱ የተገለጠው ቃል ነበር፡ የእግዚአብሔር ቃል ትርጓሜ እርሱ ነበር፡ ምክንያቱ እንዲህ ብሏልና፦ “በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።” ይኸው ነው። እሱ—እሱ የቃሉ ትርጓሜ ነበር። አሁንም በዚህ ዘመን ዳግም-የተወለደ ወንድ እና ሴት የእግዚአብሔር ልጅ ሁሉ የዘመኑ የቃሉ ትርጓሜ ነው። በሰው ሁሉ የምትነበቡ፡ ደብዳቤዎች ናችሁና። አዎን።

51 የተናገረውን፡ አስተውሉ፦ “የባላንጣ ትምህርት እንደ አስተምህሮ እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል። የባላንጣ ትምህርት እንደ አስተምህሮ፡ የሰው ትምህርት፡ የሰው ስርዓት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነገር፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል በማስተማር።”

52 ይሄውላችሁ፡ እያንዳንዱ ዘመን ፍሬ ያፈራል፡ በየዘመኑም እንዲሁ ነበረ፡ እኛም ከዚህ አናመልጥም። በተለይ ዘመናችን፡ የዓለም መጨረሻ ከመሆኑ አንጻር፡ ሁሉንም ዘመናት በአንድ ላይ ያገናኘ ትልቅ ዘመን ነው። በምድር ታይቶ የማያውቅ ትልቁ የባላንጣ ዘር፡ አሁን በምድር ፊት አለ። የባላንጣው ዘር በሌሎች ዘመናት ለነበሩት ከእግዚአብሄር አለያይቶ ጣኦታት እንዲያመልኩ ሲያደርጋቸው ነበር። በዚ ዘመን ግን ኢየሱስ በማቴዎስ 24:24 የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፡ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ እንደሚመሳሰሉ ተናግሯል። ስለ ባላንጣው ስንነጋገር! አቤት፡ ብልጣብልጥ ነው። ቃሉን በትክክል እንደሚያስተምር የሰነመሎኮት ሊቅ፣ የሰነመሎኮት ዶክተር አዋቂ ሆኖ ሰይጣን በህዝብ ውስጥ ገብቷል። ኢየሱስ ተናግሯልና። ነገር ግን ጠብቁት ብቻ፡ እንዲህ ይላል፡ “ይሄ እንደዚህ ማለቱ አይደለም።” የሚልበት፡ ቦታ፡ ይኖረዋል። ኦህ፡ አዎን፡ ነው፡ እንጂ፡ አያችሁ፡ እግዚአብሄር ተናግሯልና።

53 ያደረገውን ተመልከቱ። ይህ ራሱ የባላንጣ ዘር የእግዚኣብሄርን ቁጣ በኖህ ዘመን ላይ አወረደ፡ እግዚአብሔር እንደሚባላ እሳት ነብዩን ልኮ ህዝቡን፡ ንስሐ ግቡ እያለ በሚሰብክበት ወቅት፡ የባላንጣው ዘር ሰጥሞ ቀረ። ከዛስ በኋላ ሰይጣን ምን አደረገ? ወድያው ተነሳና፡ ዘሩ እንደገና፡ በካም ላይ መዝራት ጀመረ። ይህ እውነት ነው።

54 ቀጥሎ ሙሴ መጣ፡ የእስራኤልን ልጆች በምድረበዳ ልያሻግራቸው፡ ይህ ታላቅ ነብይ ተነሳ። ምን ሆነ? ሙሴ፡ ታላቁ የእግዚአብሔር ነቢይ ፍጹም እውነት፡ የተረጋገጠው እውነት ይዞ መጣላቸው። ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገረ። እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንደተነጋገረ አረጋገጠለት። ያኔ የነበሩ ሰዎች፡ ካህናት፡ የራሳቸውን ሐይማኖት፡ የራሳቸው ባዕዳዊ ስርአት፡ የራሳቸው ቅርጽ እና ሌላም ሁሉ ነበራቸው፡ ሙሴ ግን የእግዚኣብሄርን ቃል ፍቺ በመሆን በመካከላቸው በጽናት ቆሞ ነበር። ያንን አትርሱ! ሙሴ እግዚአብሔር የገባውን የተሰፋ ቃል ትርጉም ነበር። አደርጋለሁ ብሎ ተናግሯል፡ የእግዚአብሔር ትርጓሜ ነበር።

55 ከዚያስ ምን ሆነ? ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ ቤተክርስትያን፡ በእግሯ ከግብፅ ወጣች፡ በኋላስ ምን ሆነ? ሰይጣን ተቃርኖ ባለው ሰው፡ በልዓምን ይዞ፡ በሁለተኛው ቃየን መጣ፡ በመካከላቸውም የሚቃረን ነገር ዘራ። ይህም

እውነት እንደሆነ እናውቃለን። ያ በልዓም፡ የበልዓም ትምህርት፡ "ሁላችንም አንድ ነን፡ እናንተ የምታመልኩትን ያው አምላክ እኛም እናመልካለን፡" ነው፤ በመሠረታዊነት፡ ትክክል ነበር፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ያቀረበውን መሥዋዕት፡ በሰባት መሠዊያዎች ላይ፡ ሰባት አውራ በጎች፡ ሰባት ወይፈኖች አቅርቦ፡ ሙሴ በምድረ በዳ እንዳደረገው ፍጹም በሆነው አሰራር፡ በትክክለኛ አደራረግ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ። ተመሳሳይ ግን አልነበሩም! ይህም ወደፊት ሊሆን ያለውን ለእኛ ጥላ ነው። አሁንም፡ ቃየን፡ እንደገና... በለዓም በተባለ ሰው ራሱን ገለጠ። እግዚአብሔርም ሙሴ በተባለ ሰው ራሱን ገለጠ፡ ራሱን፣ ተሰፋ ቃሉን፣ በሰጋ ለባሸ እያስተዋወቀ፡ ቃሉን በሰጋ ለባሸ በኩል ተረጎመ። ተቃራኒውም ያኔ ተነሳ።

56 በይሁዳ ጊዜም እንዲሁ አደረገ፡ በዚያም ከባላንጣነቱ ጋር ተገለጠ።

57 አሁንም፡ አስታውሱ፡ ያኔ የነበረው ህዝብ ያመነው ሐጢአት፡ ይህም "ሁላችንም አንድ ነን፡ እኛም እናንተ የምታመልኩት አምላክ፡ እናመልካለን፡ በአንድ ቤተክርስትያን መሆን ይገባናል፡ አንድ ህዝብ እነሁን፡" ያሉትን እስራኤላውያን ሐጢአታቸው ፈጽሞ አልተሰረየላቸውም! ኢየሱስ እራሱ፡ እንዳለ፦ "ሁሉም በምድረባዳ ጠፉ!"

58 ከሶስቱ በስተቀር ሁሉንም ጠፉ። ጸንተው የቆሙትና የተሰፋውን ቃል ያመኑት እነሱ ብቻ ናቸውና። ሰሰነፎቹ "ከአቅማችን በላይ ነው፡ ምድሪቱን መውረሰ አንችልም፡" ወዘተረፈ፡ ባሉ ጊዜ፡ ካሌብ እና ኢያሱ ግን ህዝቡን አረጋግተው፡ እንዲህ አሉ፦ "ምንም ቢበረቱ ግድ አይሰጠንም፡ እግዚአብሄር ቃል ገብቶልናልና! ሄደን ለመያዝ ሙሉ አቅም አለን አሉ!"

59 አሁንም እኛ መለኮታዊ ፈውሰን፣ እና የመንፈሰ ቅዱሰን ጥምቀትን እየሰበክን፣ ከዓለም ነገሮች ሊለየን የሚችል የእግዚአብሔር ኃይል አሁንም አለን። እግዚአብሔር ተናግሯልና! የሐዋርያዊ ዘመን አልቆመም፡ አይቆምም፡ ይቀጥላል።

60 ስለዚህ፡ አሁንም ራሱ የባላንጣ ዘር ዘሪው እናገኛለን። አስታውሱ፡ ያን ሐጢአታቸውም ፈጽሞ አልተደመሰሰላቸውም። አሁንም፡ ያኔ ካልራራላቸው፡ የዘመናት ሁሉ እውነተኛው ዘር—በአንድነት በሚገለጡበት በዚህ ዘመንሰ፡ ወንድሜ?

61 በለዓም ያደረገውን ይህን ታላቅ ነገር አስተውሉት፡ ይህ ነገር ሄዶ ሄዶ፡ በመጨረሻ በአስቆሮቱ ይሁዳ፡ እና በኢየሱስ መምጣት—ፍጻሜውን አገኘ። ምን ነበር? ይሁዳ እና ኢየሱስ በትክክል የቃየን እና የአቤል ምሳሌ ነበሩ። ይሁዳ ሃይማኖተኛ እንደነበረ፡ ቃየንም ሃይማኖተኛ ነበርና። ቃየን መሠዊያን ሠራ፡ መሰዋዕትንም አቀረበ፣ እግዚአብሔርን አመለከ፡ ልክ እንደሌላኛው እርሱም ከልቡ አቀረበ። ነገር ግን፡ ተመልከቱት፡ የቃሉ ምንነት መገለጥ አልነበረውም። አዳምና ሔዋን አፕል ወይም አንዳንድ ፍሬዎች የበሉ መሰሎት ነበርና። ቃየን... አቤል ግን፡ ይህ ስህተት እንደሆነ በመገለጥ አውቋል፤ ያሰወጣቸው ደም ስለነበረ፡ ጠቦት ሠዋ። እግዚአብሔርም መሥዋዕቱ ትክክል መሆኑን መሰከረለት። በዚህም ቀንቶ ወንድሙን መግደል ፈለገ። በጉ በሞተበት በዚያው መሰዊያ መሰዋዕቱ በሞተበት መሰውያ ላይ፡ ወንድሙን ገደለ። እንዲሁም የአስቆሮቱ ይሁዳ ኢየሱስ ክርስቶስን በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ

አሳልፎ ሰጠው፣ ቃየን አቤልን እንደ ገደለው ገደለው። ቃየን፡ የባላንጣው ዘር ነውና።

62 ቅጥረኛው ነቢይ፡ በልዓም ግን፡ ከዚህ በተሻለ ማወቅ ያለበት ሰው ነበር። እግዚአብሔርም በምልክቶችና በድንቆች፡ በማይታወቅ ልሳኖችም በምትናገር በቅሎ ሳይቀር አስጠነቀቀው፡ አሁንም ግን እንዲሁ ተነዳ። የባላንጣ ዘር ዘሪ—ሊሆን ተወልዷልና።

63 ኢየሱስም ለብ ያለውን ይህ ዘመን እስከ ዛሬ ከነበሩት ዘመናት ሁሉ ይልቅ እሱን ከቤተክርትያን ያሰወጣው፡ የሎዶቅያው ቤተ ክርስትያን ዘመን፡ በታላቅ ባላንጣነት እንደሚገባደድ፡ ተንብየዋልና፡ ይህ ዘመን ሌላ አይደለም፡ የባላንጣው ነው! በእርግጠኝነት፡ ነው። በዚያ ዘመን ያበቃል።

ይህም ቃየን እና አቤል እንደገና ቀራንዮ ላይ ናቸው።

64 አሁን አስተውሉ፡ ልክ ኢየሱስ እንዳረገ፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደገባ፡ መንፈስ ቅዱስ ተላከ። ትናንት ማታ እንደተናገርነው፡ የቃሉ ሕይወት-ሰጪ የሆነው ዘር፡ እርሱ ነው። ቃሉን የሚያነቃው እርሱ ነው። **ማንቃት** ማለት "ህይወት መሰጠት።" እውነተኛው መንፈስ ቅዱስ ህያው የሆነውን ቃል ብቻ ወደ ህይወት ያመጣል። ለሐይማኖቱ ሰርዓት ህይወት አይሰጠውም፡ በጭራሽ፡ ምክንያቱ ከአዋልድ አይደለምና። እርሱ አምላክ ነውና፡ የእግዚአብሔር ቃል ህይወት እሱ ነው። አያችሁ? ለአካሉም ህይወትን ይሰጣል።

65 እነርሱ ይህን ሲያደርጉ፡ አስታውሱ። ከዚያም፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ ዮሃንስም—ለልጆቹ ተናግሯል፦ "ልጆች ሆይ፡ ወደ ዓለም ስለሚመጣው የክርስቶስ ተቃዋሚ ስምታችኋል፡" "አሁንም በዓለም ውስጥ አለ፡ በማይታዘዙ ልጆች ውስጥ ይሰራል፡" አላቸው። ይህም የሆነው፡ መንፈስ ቅዱስ ከወረደ ከሰላሳ ዓመታት በኋላ ነው። ሲመጣም፡ እውነተኛው ዘር፡ ለዘሩ እውነተኛው ሕይወት-ሰጪ፡ የሆነ መንፈስ ቅዱስን እናገኛለን፡ ከዛ በኋላ ተቃራኒው እንደገና ይመጣል። አስተውሉ፡ እንዲሁ ይቀጥላል። ሌላው...

66 እውነተኛው ቃል ምስክር አለው፡ የጥንት ነቢያት ሁሉ በሄዱበት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት መሆኑን ምስክር ነበራቸው። **የኒቂያ ጉባኤን፡** ወይም **የቅድመ-ኒቂያ ጉባኤን፡** እንዲሁም ስለ አስራ አምስቱ ቀናት ደም አፋሳሽ ፖለቲካ ያነበበ ካለ፡ የሮማውያን ምናምንቴዎች ከቤተ ክርስትያኒቱ የሐይማኖት ተቋም ለማቋቋም ያሰቡ ነበርና። ነብያት፡ የበግ ለምድ ለብሰው፡ ቅጠላ ቅጠል እየተመገቡ ሲመጡ፡ ለቃሉ ቆሙ! እሱስ ምን አደረገ? እንደ ቃየል፡ እንደ አቤል መሆን ተገባው፡ አንዱ ሊሞት የግድ ሆነ። አዎን፡ የግድ ነው። ቃሉም በህዝብ መካከል ያለውን ተጽእኖ አጣ፡ ሁሉም እውነተኛውን ቃል አልፈለጉም በምትኩ የቀደመችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ ዶግማዎች ተቀበሉ። ጳጳሰ ሾሙ፡ ቢሾፕ ሾሙ፡ **ይህን፡ ያንን፡ ሌላውን** ሾሙ። እውነተኛው የጴጥሮስ፡ እና የ—የ—የማርያም፡ እና—የሌሎች ትርጉም ወሰደው፡ ክርስትና ከሚባለው-ሐይማኖት ጣኦታትን ሰሩ፡ የአረማውያን በዓላት ሰሩ። ይህስ ምን ነበር? የተቃራኒው ዘር ነው! በምድር፡ ለመጀመርያ ጊዜ፡ ቤተ ክርስትያንን አደራጁ፡ ተደራጁ። ይህስ ምን ነበር? ያንን የተቃራኒው ዘር፡ አንዱን ቀንሶ፡ ሌላ ነገር በመጨመር ማላገብ ጀመረ።

67 ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ አርብ ስጋ አትብሉ ሲባል፡ የሰማ ማን አለ? በጥልቅ ውሃ ከማጥመቅ ይልቅ፡ መጽሓፍ ቅዱስ፡ ውሃ እርጩባቸው ሲል፡ የሰማ ማነው? "ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፡" ሌላ ሌላ ነገሮች፡ ሲል የሰማ ማን ነው? ትርጉም አልባ የሆነውን፡ የማይረባ የፕሮተስታንቶቹስ ቢሆን? እንስራ ጀበናን ቆሻሻ ነሽ አትላትምና። ትክክል! በቃ፡ በትንሹ የሳተ ሁሉንም እንደሳተ ነው! እግዚአብሔር ሰራውን በድርጅት ይሰራል ያለው ማንነው? የትኛው ህብረት ነው ተደራጅቶ በህይወት የቆየው አሳዩኝ። ወድያው ይሞታሉ እንጂ፡ ፈጽመውም አይነሱም! ይህ ጊዜ የሆነ ነገር የሚሆንበት ጊዜ ነው፡ እግዚአብሄርም የሚንቀሳቀስበት ጊዜ ነው። በህዝቡ መካከል የነበረውን መነቃቃት ገድለውታልና።

68 ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ሆኗል። ተጽእኖውን አሳጡት፡ "አይ፡ እነዚህ ሆሊ-ሮለሮች፡ ተራዎች ናቸው።" እንዴት፡ ለምን፡ ተቃርኖ ነው! ከቃሉ ጋር ፊት ለፊት ተገናኙና መርምሩ፡ እግዚአብሔር የራሱን ቃሉን እንደሚተረጉም እዩ። እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆችን ሊያስነሣ ይችላልና። ኣሜን።

69 በቀደምት ክርስትያኖች ላይ ቃሉ ምስክር ነበረው፡ እግዚአብሄርም ከብዙ ይታደጋቸው ነበር፡ ከበሽታ፡ በመካከላቸውም ነብያት ነበሩ፡ ልሳን ይናገራሉ፡ ይተረጉሙታል፡ በየዕለቱም እውነትነቱን የሚያረጋግጡበት መልዕክት ይሰጣሉ። ይሄን ሁሉ እያዩ ግን ምስክር ያለውን ቃል መግፋት ጀመሩ፡ ከቃሉም ይልቅ የሐይማኖት ተቋም መረጡ። እሷ የድርጅቶች ሁሉ እናት ናት።

70 አሁን ሁለቱም ሙሉ በሙሉ አደጉ። ሁለቱም እንደገና መዝራት ጀመሩ። ሞተ፡ ነገር ግን በሉተር ዘመን እንደገና አበቀለ፡ እዚህ ቁርስ ከጥዋቱ አንደኛው መልእክት ተረድተናል። በሉተር ዘመን በቀለ። ከዚያስ ምን አደረጉ? ያ ታላቅ ሰው ከሞተ በኋላ፡ ወዲያው ድርጅት አቋቋሙ።

71 በቀለ። እንደገና በጆን ዌስሊ ዘመን፡ አንግሊካውያን፡ ዘላለማዊ ደህንነት ከሚሉት ነገራቸው ጋር፡ ነገር ሁሉ ከሞላ ጎደል ዩኒቨርሳሊዝም ወደሆነው ስፍራ አሰረውት ነበርና፡ ምን ሆነ? እግዚአብሔር ጆን ዌስሊ የተባለውን ሰው አስነሰቶ፡ ሁሉንም አጠፋ። እና እሱ ልክ እንደሞተ፡ አሰበሪ ሌሎቹ ሁሉ እንደሞቱ፡ ምን ሆኑ? ተደራጁ፡ የተለያዩ ዓይነት ሜቶዲስቶች አሉ። ከዚያ ሌሎች መጡ፡ እነ አሌክሳንደር ካምቤል፡ ጆን ሰሚዝ፡ እና-ሌሎች አብረው መጡ።

72 በመጨረሻም፡ ከነዚህ ሁሉ በኋላ፡ ጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ ፈንድቶ ወጣ። ከዚያስ ምን ሆኑ? በትክክል ሮጠው ነበር፡ ታዲያ ማን አዚም አደረገባችሁ? ወደ መጣችሁበት ጭቃ ተመለሳችሁ፡ ቁልቁል ተንሸራትታችሁ በቃሉ ላይ አመቻመቻችሁ፡ ወደ ተቃራኒው ዘር ተቀላቅላችሁ ተቋም ፈጠራችሁ። እግዚአብሄር አዲስ ነገር በላከ ቁጥር፡ አትቀበሉትም። እውነት ነው! ተቃርኖ እንደገና! ባለፈው ቀን የተናገርኩትን አስታውሱ፡ የመጀመርያዋ ቡቃያ ከስር በወጣች ጊዜ፡ ቀጥታ ወደ ቅጠል ታድጋለች፡ ከቅጠልም ዝራረት ታወጣለች፡ ወድያውም አገዳ ትሆናለች፡ ከዛ ትበቅላለች። ትንሿ የሰንዴ ቅርፊት እህሉን ትመስላለች፡ እኛም እንዲሁ እናስባታለን፡ ስትከፍቱት ግን፡ በውስጡ እህል አይኖረውም። እህሉ እንዲበቅል ደጋፊ ብቻ ነው፡ ደግሞም ይሞታል፡

ሕይወትም ከእርሱ ወጥታ ወደ እህል ትገባለች። ልብ በሉ፡ ስለዚህ የዘሩትን አብያተ ክርስቲያናት...

73 ቤተ ክርስትያን ተብዬው-ሁሉ፡ የእኛም ጴንጤቆስጤዎች ሳይቀሩ፡ ሁላችንም እንወጣለን፡ እርካታ ስለማናገኝባቸው፡ የራሳችን ቡድን እንመሰርታለን። **ይሄም** አለን፡ **ያም** አለን፡ ሁሉም ይበቅላሉ፡ ሌሎችም የተለያዩ ቡድኖች አሉ። አንዱ ይነሳና፡ "ከነጭ ደመና ጋር ይመጣል፡" ይላል። ሌላኛው "አይ-አረ፡ በነጭ ፈረስ ይመጣል፡" ይላል። "እሺ፡ ሁለት ቡድኖችን እንሰራለን።" አያችሁ፡ ምንድን ነው? ይህ ባላንጣውን መዝራት ነው! እሱ ሲመጣ፡ ምንም ይሁን፡ ሲመጣ የገዛ ቃሉን ይተረጉማል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ እንጠብቀው። ይሄን ያዙት... ስለዚያ ካወራችሁ፡ የዘመኑን መልእክት ገና አልተቀበላችሁም። እግዚአብሔር ወደፊት ወደሚያደርገው፡ ወይም ከዚህ በፊት ወዳደረገው ሁልጊዜ እንጠቁማለን፡ አሁን የሚያደርገውን ግን ችላ እንለዋለን። በውስጡ ባላንታዎችን የምናገኝበት መንገድ ይህ ነው።

74 ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችንን ስናይ፡ አብያተ—ክርስቲያናቶቻችን በሙሉ ነፋስን ዘርተው፡ ዐውሎ ነፋስንም ሲያጭዱ እያየን ነው። የጸሎት ስብሰባዎች የሉም፡ አገልግሎቶች እንደ ድሮ የሉንም። ምንድነው ችግሩ? በሁሉም ቡና ቤቶችን አስንቀናል። የኛን የጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያንን፡ ተመልከትዋት፡ ጸጉራቸው-በቆራረጡ ሴቶች ተሞልታለች። አይፈቀድም ነበር። ፊታቸው በመዋብያ የተለቀለቀ፡ ጥፍራቸው ቀለም መቀባት፡ የተለያየ ነገሮች፡ እንደነ ሪክስ እና... መሰሎቹ ዓይነት፡ ሶስት አራት ጊዜ ያገቡ ወንዶች፣ እና ዲያቆናት ይይዛሉ፡ አቤት፡ ምን አይነት ባላንጣ ነው! ቱከት ነው! እንዲህ የሚያደርጉት እንዴት ነው? እግዚአብሄር በቤተ ክርስትያኑ እንዲህ ስለማያደርግ፡ ለመግባት ወደሚያመቻቸው ድርጅት ይሄዳሉ። ከድርጅት ያባርሩኛል ብሎ ስለሚሰጋ፡ በፍርሃት ማንም ምንም መናገር አይችልም። እግዚአብሄር ሆይ፡ ከእግዚአብሄር እና ከቃሉ በቀር ከምንም ጋር ያልተገናኙ ሰዎችን ሰጠንና፡ እውነቱን በራሱ ይገልጠዋል። በትክክል የሚያስፈልገን ይህ ነው። እኛ ግን ምን አደረግን? ባላንጣን ዘራንበት። ነፋሶችን ዘርተናልና፡ አሁን አውሎ ነፋሱን እናጭዳለን።

75 አሁን ለመቃጠል እየተሰበሰቡ መሆናቸውን ልብ በሉ። ኢየሱስ ያለውን፡ ልብ ብላችኋል፡ "አስቀድማችሁ፡ በየነዶው፡ አንድ ላይ ስብሰቧቸው፡ ነዶዎቹንም ሁሉ አንድ ክምር ላይ አስቀምጧቸው፡ እኔም አቃጥላችኋለሁ።" ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ሉተራን፣ የሚባሉ ትንንሽ ነዶዎች አሉ፡ እነዚህም ሁሉ ወደ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ውስጥ እየተሰበሰቡ ይገኛሉ። ይሄስ ምን ማለት ነው? "መጀመሪያ ስብሰቧቸው!" ሃሌ ሉያ! ልብ ብላችኋል? መጀመሪያ እንክርዳዱን ይሰበሰባል፡ ከስንዴው ያላቃቸዋል፡ ይለያቸዋል፤ "በአንድነት ሰብሰቧቸው እና ይቃጠሉ።" ባነሳሷቸው ነገሮች... በሰዎች መካከል አለመግባባትን ስለዘሩ፡ ሁሉም በእግዚአብሔር ፍርድ ይቃጠላሉ፡ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉንም ክደዋል፡ ከአንድ ዶግማ የተቀዳ፡ ሰው የከተባቸውን የሐይማኖት ሰርዓት ወደ እግዚአብሔር ቃል ለማቀላቀል፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይክዳሉ። አይሰራም። ባላንጣነት ነውና።

76 ታላቅ ነቢይ፡ አሞጽ፡ እንዳደረገው፡ ወደዚያች ከተማ ወርዶ፡ እንደተናገረ፡ እኔም ድምጼን አሰማለሁ፡ "ነብይ አይደለሁም፡ የነብይ ልጅም አይደለሁም። አንበሳ ሲያገሳ ግን፡ የማይፈራ ማን ነው?" "እግዚአብሔር ተናግሮስ፡

ትንቢት የማይናገር ማን ነው? ” ብሏልና፤ በትውልዱ ላይ ፍርድን ተናገረ፡ “እናገለግለዋለን የምትሉት አምላክ እራሱ ያጠፋችኋል፡” አላቸው።

77 እናንተም ይሄን ያዙ፡ ቴፕ ላይ ተቀድቷል፡ አስታውሱትም። ያ አምላክ... እነዚህ ሰዎች ወደ ትልቁ—የዓለም አብያተ ክርስትያናት ጉባኤ ወደ ተባለው ትልቅ መኸር እየተሰበሰቡ ይገኛሉ፡ እናንተም ትገቡበታላችሁ። ከዛም መውጣት አትችሉም። በግልህ ሄደህ ትርቃለህ፡ ወይም አብረህ ትቀላቀላለህ። መሐል ሰፋሪ የለም። የአውሬው ምልክት እሱ ነው። ተቃራኒው የሌለው ሁሉ፡ ምልክቱን ያልተቀበለ፡ ሊገዛም ሊሸጥም አይችልም። ከዚያ ራቁ! አምልጡ ውጡ! ሽሹት! ከመካከሏ ራቁ! እናገለግለዋለን ብለው የሚሉት አምላክ እራሱ ይደመስሳቸዋልና። ታላቁ የፍቅር አምላክ...

“እንዴ፡ ኢየሱስ ራሱ አንድ ሁኑ ብሎን የለምን፡” ይላሉ።

78 “ሁለቱ ካልተስማሙስ፡ ሁለቱ እንዴት አብረው ይጓዛሉ? ” ደግሞ ብሏል፤ እርሱ ያለው “አንድ፡” እንደ እሱ እና እንደ አባት አንድ ነው። አባት ቃል ነው፡ እሱ ደግሞ የተገለጠ ቃል ነው። ከአባት ጋር “አንድ” ነበር፡ ምክንያቱ የተገለጠው የእግዚአብሄር የተሰፋው ቃል እሱ ነበረና። ዛሬም ሆነ፡ ሌላ ቀን እንዲሁ ነው። የስ፡ ስር። እግዚአብሔር አንድ ነው። እኛም አንድ እንድንሆን ይፈልጋል።

79 **ያኛው** በድንግልና መወለዱ የሚክድ፣ መለኮታዊ ፈውስ የሚክድ፣ **ያኛው** ይሄን የሚክድ፣ **እነዚህ** እንዴት አንድ ይሆናሉ፡ **ያኛው፡ ይሄኛው** ሁሉ፡ እንዲህ ተመሰቃቅለው እንዴት ይሆናል? አንዳንዶቹ እንደውም በእግዚአብሄር አያምኑም፣ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እመኑ፤ የሚያምኑት ዮሴፍ ልጅ እንደነበረ ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ **እንደተጠራ** እመኑ። በትክክል። የሉተራን፡ እና የዝዊንግሊ መንታ ወንድም፡ ፍጹም የሆነ መልካም ሰው ነው፡ ብለው ያምናል። ክርስትያን ሳይንሶችም እሱ ተራ ሰው፡ ተራ ነብይ እንጂ፡ መለኮታዊ አልነበረም ይላሉ። እንዴ፡ መሎኮት ካልነበረ'ኮ፡ እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ዓለም ከመጡት አሳቾች ከፍተኛ አሳች ነው ማለታቸው ነው። እግዚአብሄር ነበረ እንጂ ካልሆነ ግን ተራ ነበረ። እርሱ ግን መለኰት ነበረ! አምላክ ነበረ፡ ስጋ ሆኖም፡ በመካከላችን የእግዚአብሄር ልጅ በሚባል አካል አደረ። በርግጠኝነት፡ እንዲሁ ነበረ።

80 አሁን ባላንጣ ገብቶ አይተነዋል። እዚሁ እንዳለ እናውቃለን፡ ይሄንን ማንም አይክድም። ኦ፡ ማይ! ብቻ ልብ በሉ። እናመልከዋለን የሚሉትን አምላክ ራሱ ያንኑ ጎራ ሲያጠፋ። አሰቡት እስኪ።

81 እግዚአብሔር ዘሩን ዘራ። ወደ ጸሎት መግባት ስላለብን፡ እየጨረስኩ ነው። እግዚአብሔር ዘሩን ዘራ፡ ዘሩም ክርስቶስ ነው። ጌታ ቢፈቅድ፡ ከጥቂት ምሽቶች በኋላ፡ እግዚአብሔር ሰሙን ሊያስቀምጥበት በወደደው ነገር ላይ እሰብካለሁ፡ ምናልባት ጊዜ በማገኝበት በቁርስ ክፍለ ጊዜ እሰብካለሁ። ልብ በሉ፡ ብቸኛው ማምለጫ እሱ ነው። እውነተኛ አቅም ያለው እሱ ነው። ከጎኑ ሌላ የሌለው፡ አንዱ አምላክ እርሱ ነው። “አምላክ፡ እኔ ብቻ ነኝ፡” ብሏልና። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “ትእዛዚቱም እንዲህ ናት፤ እስራኤል ሆይ ስማ፡ ጌታ አምላካቹ፡ አንድ አምላክ፡ እኔ ነኝ። እኔ እርሱ ነኝ። ሌሎችን ለምን ትሻላችሁ? ሌሎች መጡ... እኔም በአባቴ ስም መጣሁ፡ አልተቀበላችሁኝምም። ሌላው ግን በራሱ ስም ይመጣል፡ እናንተም ትቀበሉታላችሁ።” በኒቅያ ያደረጉትም ይኸው ነው።

“ክርስቲያን ነህ? ”

“ባፕቲስት ነኝ።”

“ክርስቲያን ነህ? ”

“እኔ ጴንጤ ነኝ።”

“ክርስቲያን ነህ? ”

“እኔ ሜቶዲስት ነኝ” ሌላ ሰያሜ።

82 “ኢየሱስ ክርስቶስ፡” ወደ ሚባል ስም ሲመጡ ግን፡ ከስሙ የቻሉትን ያህል ርቀት ይሸሻሉ። እርሱ ራሱ ቃል ስለሆነ፡ ቃልም እራሱን ስለሚተርክ፡ ፈጽመው አይፈልጉትም። ልብ በሉ፡ ብቸኛው ማምለጫ እሱ ነው! መጽሓፍ ቅዱስ፡ የሳሮን ጽጌረዳ ይለዋል። (በመጽሓፍ ቅዱስ) የሚገኙ የእግዚአብሔር መዓርጎች በሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው። እሱ አልፋ፣ ኦሜጋ፣ የመጀመርያ እና የመጨረሻም ነው፡ የነበረው፣ ያለው፣ የሚመጣው፣ የዳዊት ልጅ እና ሥር ነው፡ ልጁ እና ሥሩ ነው፤ የንጋት ኮኮብ፣ የሳሮን ጽጌረዳ፣ የሸለቆው አበባ፣ አልፋ፣ ኦሜጋ፣ አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ! በእኛም ዘንድ ለማደር በስጋ የተገለጠ የጅሆቫ ሙሉ መገለጫ እሱ ነው። በትክክል እንዲሁ ነው።

83 የሳሮን ጽጌረዳ እሱ ነበር። የሳሮን ጽጌሬዳን ምን ያደርጉታል? ከውስጡ መልካም የመዐዛ ሽታን ለማግኘት፡ ይጨምቁታል፡ ያሹታል። መልካም ጽጌረዳ መልካም ነገር እንድያወጣ ጽጌረዳው ይጨመቃልና። እርሱም ውብ ሕይወት ነበረ፡ እንደ እሱ ውብ ሕይወት አልነበረም፡ በቀራንዮ ላይ ግን መጨመቅ ነበረበት።

84 እያችሁ፡ ከሳሮን ጽጌሬዳ የተገኘውን ጥሩ መዓዛ ወሰደው—አሮንን ይቀቡታል፡ በመጋረጃው በኩል፡ እግዚአብሄር ወደ ሚገኝበት ወደ ቅዱስ ስፍራ ለመግባት ያንን መቀባት ነበረበት። በየዓመቱ በሚረጨው በምህረት ዙፋን ፊት ለመቅረብ፡ በሳሮን ጽጌረዳ መቀባት ነበረበት። የበጉን ደም በፊቱ ይዞ፡ እንዲሁም በበጉ-ከተረጨ በኋላ፡ ለጌታ መልካም የመዓዛ-ሽታ ለመሆን፡ ያንን ቅባት በላዩ ላይ ይቀባል። ልብሱ ላይም ሮማኖች እና ቃጭሎች አንጠልጥሎ፡ “ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና ለእግዚአብሔር፡” እያለ ልዩ እንቅስቃሴ ይጫወታል።

85 ልብ በሉ፡ የሳሮን ጽጌረዳ፡ በህዝቡ ላይ የተቀባ፡ ጣፋጭ-ሽታ እሱ ነው። ከሳሮን ጽጌረዳ፡ ከቃሉ ቅባት እንጂ፡ የሐይማኖት ስርዓት እና ሌላ ተቀብታቹ፡ በፊቱ መቅረብ አትችሉም። ደግሞ የሸለቆው የሊሊ አበባ እሱ ነውና።

86 አሁን፡ ኦፕየም ከምን ይገኛል? ሊሊን ወሰዳችሁ ስትጨምቁት፡ ኦፕየም ታገኛላችሁ። ዶክተሮች በላቦራቶሪአቸው ይጠቀሙበታል። የተረበሸ እና የተወዛገበ ሰው፡ ወይም የተረበሸች፡ ማበድ ማበድ ያላት ሴት ውሰዱ፡ ወለሉ ላይ እየሄደች ትጮኻለች፡ ጭንቀት ውስጥ ነች፡ ዶክተሩ ከሊሊው ኦፕየም ወስዶ፡ እጅዋ ላይ ወይም ደም ስርዋ በሚገኝበት ስፍራ፡ ሲሰጣት ትንሽ ረጋ ያደርጋታል። ለተወሰነ ጊዜ ያረጋጋል። ልክ ኦፒየሙ እንዳለቀ፡ እንደገና ይጀምራቸዋል፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ የከፉ ይሆናሉ።

87 ወዳጆች ሆይ፡ እላችኋለሁ፡ ይህ ግን እኔ የማውቀው ትክክለኛው የሸለቆው የሊሊ አበባ ምሳሌው ነው። እሱ የሸለቆ የሊሊ አበባ ነው። በቀራንዮ

ላይም ተጨመቀ። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን። በዚያም፡ አበቦች በሚጨመቁበት ሂደት ውስጥ፡ እሱ አበባ ነበር። እስከ አሁን ድረስ ከበቀሉ አበባዎች ሁሉ ይልቅ ድንቅ አበባ፡ የሸለቆው የሊሊ አበባ፡ እና የሳሮን ጽጌሬዳ እሱ ነው። አሁንም ዛሬ ማታ፡ በሰማይና በምድር መካከል ተዘርግቷል፡ መስቀሉንም፡ እምናለሁ፡ ያኔ የሆነው፡ ማለት፡ የዓለምን ኃጢአት—ለማስወገድ እና ፈውስን ወደ ዓለም ለማምጣት እንደሆነ እምናለሁ። መፅሐፍ ቅዱስም ትናንትናና፣ ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው እንደሆነ ተናግሯል።

88 ወዳጆች ሆይ፡ እግዚአብሄር፡ በምድረ በዳ፡ ለሙሴ—የራሱን ምሳሌ የሚሆነውን የናስ እባብ እንዲሰቅል ነገረው። ያ ናስ የሐጢአት መፈረድ የሚያስረዳ ነው፡ እባቡ ደግሞ፡ **የናስ እባብ ደግሞ** "ሐጢአት ፍርድ ማግኘቱን" ያሳያል። ይህም መሰዋዕቱ የሚቀርብበት መሠዊያ ከናስ የተሰራ እንደነበረ ነው፡ **ናስ** ማለት "መለኮታዊ ፍርድ፡" ያስረዳል። ኤልያስም አሻቅቦ አየና ሰማያት እንደ ናስ ሆኑ አለ፡ ከእግዚአብሔር ወደ ኋላ በተመለሰ በማያምን ሕዝብ ላይ ይህ መለኮታዊ ፍርድ ነው። ናስ ፍርድን፡ መለኮታዊ ፍርድን ይወክላል። እባቡም አስቀድሞ የተፈረደበት ኃጢአት ይወክላል፤ ኢየሱስም ስለ እኛ ኃጢአትን በመሆን፡ የእግዚአብሔርን ፍርድ በእርሱ ላይ የወሰደ ያንን እባብ እሱ ነበር። እርሱ ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ፡ የደህንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።

89 አቤት፡ እግዚአብሔር ዛሬ፡ ለእናንተ ያዘጋጀው፡ ሙሉ ኦፒየም ይዟል። ታመህ ሰቃይ ላይ ያለኸው፡ ክርስትያን ወዳጄ ሆይ። አቤት፡ አንተ ደክሞሃል፡ ከአቅምህ በላይ ሆኖብሃል። ከዚህ በላይ መቋቋም ተሰኖሃል፡ አሁን በምንኖረው ዘመናዊው ዓለም—ለመወሰድ ተቃርባሃል።

90 ዛሬ ማታ፡ በ '55፡ **ላይፍ ላይን** ላይ፡ ሩስያ—ያለችውን፡ ሰምታችኋል፡ "መላ ዓለሙን እንደሚቆጣጠሩ" ሰማችሁ? እንዲህ ከመሆኑ በፊት፡ ንጥቀት ይሆናል። ምን ያህል እንደተቃረበ፡ አያችሁ ወገኖች? በቃ በደጃፋችን ነው።

91 ዛሬ ማታስ በፍጹም ልባችሁ አትፈልጉትም? የሸለቆው የሊሊ አበባ እሱ ነውና፡ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው። ሙሴ የተፈረደበት የኃጢአት ምልክት እንደሰቀለ፡ በህዝቡ መካከል እራሱን ይሰቅል—ዘንድ፡ ዛሬ እዚህ አለ። በሽታንም ጭምር እንጂ፡ ኃጢአት ብቻ አይደለም። ኢየሱስ ያለውን አስታውሱ፦ "ሙሴ የናሱን እባብ እንደ ሰቀለ፡ የሰው ልጅም ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል።" ሙሴ የሰቀለው ስለ ምን ነበር? ስለ ኃጢያት፣ ስለ አለማመን፣ እና ስለ በሽታ። ኢየሱስም፡ የተሰቀለው፡ ስለ ሐጢአት፣ ስለ ሕመም፣ እና ስለ አለማመን። ተመሳሳይ ነገር ነው።

92 አሁንም፡ ዛሬ ማታ፡ ይህን ታላቅ ባላንጣነት በገጠመን ጊዜ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ላይ... ከጌታ መምጣት በፊት፡ ተስፋ ሰጥቷል፡ ይህም የሰው ልጅ እራሱን በሚገልጥበት ጊዜ፡ በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ በዚያም ያኔ የሰው ልጅ እራሱን ለአብራሃም ተገልጦ፡ ኤሎሂም፡ አምላክ ሆኖ፡ በስጋ ተገልጦ፡ በአብራሃም መካከል እንደመጣ እና እንዳሳየው፡ ሣራ በድንኳኑ ውስጥ (ከኋላው ተቀምጣ) የምታስበውን፡ አይቶት የማያውቀውን ነገረው። ምን እንዳደረገች ነገራት... ስሟንም "ሳራ" አላት። "አብርሃምን፡" በተነሳበት

ሰያሜ—አብራም ሳይሆን፡ አብርሃም አለው። ሳራይ S-a-r-a-i፡ ሳይሆን፡ S-a-r-a-h,፡ “ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት?”

“ከኋላህ ባለው ድንኳን ውስጥ አለች፡” አለው።

93 “የዛሬ አመት እጎብኝሃለሁ፡” አለው። እሷ ግን ሳቀች። “ለምን ሳቀች?” አለው፤

94 አሁንም፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ “ይህ ታላቅ ባላንጣነት ተሰብስቦ ከመቃጠሉ በፊት፣ የሰው ልጅ ያኔ እንዳደረገው አሁንም ራሱን ይገልጣል።” ይህስ... ምንድነው? እንደገና፡ በፊታችሁ፡ መሰቀሉ ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና፣ ዛሬም፣ እስከ ዘላለም ድረስ ያው ነውና። ታምናላችሁ? ለጸሎት አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

95 አምላክ ሆይ፡ እንወድሃለን። ጌታ ሆይ፡ ቃልህ—የሚያጠግብ-ምግባችን ነው። ጌታ ሆይ፡ መኖርያችን ነውና! እንወደዋለን። አቅማችን መቼም በቂ እንዳልሆነ ይሰማናል። ጌታ ሆይ፡ እንዲህ በህብረት ስንሆን፡ በገበታህ ማዕድ ዙርያ፡ በቃልህ ሰፍራ፡ ተቀምጠን፡ በረከቱን መካፈል፡ የደምህ ዋጋ በሆነው፡ በእግዚአብሔር ልጅ ደም የተገዙ ወንድሞች እና እህቶች ሆነን መባረክ እንወዳለን። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እዚህ ተገኝተን፡ እነዚህን ምሽቶች ለታመሙ እንድንጸልይባቸው ለይተናቸዋል። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍትም “በመገረፋ ቊስል ተፈውሳችኋል፡” ተብለናል። ስለዚህ (ሐጢአቶቻችንን መናዘዝ ብቻ እንጂ) መጸለይ አያስፈልግም፡ ምክንያቱ በመገረፍህ ቁስል ተፈውሳችኋል (ፓስት ቴንስ ነው።) ኦህ፡ እንዴት ያለ የመዳን ቀን ነው! እንዴት—እንዴት ያለ የአማኑኤል ቃል ኪዳን ነው! በእርግጥ እውነት ነው።

96 አንተም እንዳልከው፦ “ጥቂት ጊዜ አለ፡ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ ምክንያቱ እኔ” (የግል ተውላጠ ስም “እኔ”) “እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም፡ እኖራለሁ” ብለሃልና። እና በዚህ በጊዜው መጨረሻ፣ ይህ ታላቅ ፍጻሜ፣ ከመፈጸሙ በፊት፡ እሳቱ በሰዶም ላይ ወርዶ የአሕዛብ ዓለም ከማጥፋቱ በፊት፡ እንደነበረው እንደሚሆን ተናግራሃልና፡ ይህም በሰዶም እንደነበረው የሰው ልጅ መገለጥ ደግሞ ይመጣ ዘንድ ነው። አባት ሆይ፡ ህዝቡ ይህንን አይሳተው።

97 እግዚአብሔር ሆይ፡ (ካጠፋሁ፡ ይቅር እንድትለኝ)፡ እንደማልጠቅም፡ እንደ ትንሽ ሰው እጸልያለሁ፡ ወደ አንተም መልሰኝ። ጌታ ሆይ፡ እወዳቸዋለሁኝና። ይሄንን ነገር እንዲያመልጣቸው እ—እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ምሽቱ ከታላላቆቹ አንድ ትሁን። የትኛውም በሽታ የታመመ፡ የተጎዳ፡ የታወረ ቢሆን፡ ሌላ ሌላ፡ እዚህ ቢኖር፡ ዛሬ ምሽት ፈውስ ይሁንለት ጌታ ሆይ። ኃጢአተኛውም ሁሉ ይዳን። አሁን በልባቸው ውስጥ፡ የማያምኑ ከሆኑ፡ በዚህ ጊዜ ክርስቶስን ይቀበሉ። ፍቀድ፡ አባት ሆይ። ሁሉም በእጅህ ነውና። በመካከላችን ስትመጣ ለማየት፡ ራሳችንን ለአንተ እናስገዛለን።

98 አንተም በቅዱስ ዮሐንስ 14:12 ላይ “በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡” ብለሃልና። ሙሴ ስለ አንተ እንደ እኔ ያለ ነብይ ይነሳል ብሎ የተናገረልህ፡ አንተ መሆንህን አውቀናል። ለብዙ አመታት ያለ ነብይ እየኖሩ፡ ባላንጣው በሁሉም ነበረ፡ የእግዚኣብሄርም ቃል ይፈጸም ዘንድ ግን የግድ ነበርና፡ ቃሉ ሰጋ ሆነ፡ ባላንጣውም እንዲሁ ሆነ። አሁንም፡ አባት

ሆይ፡ ተቃራኒው አንድ ትልቅ ክምር ሆኖ፡ እንደገና ዛሬም አይተነዋል፤ ቃሉም በተመሳሳይ መንገድ መጥቶ አይተናል። አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ባርከን። በቃልህ፡ ራሳችንን ለአንተ አደራ እንሰጣለን። ጌታ ሆይ፡ በእኛ ልታደርግ የወደድከውን ነገር ሁሉ፡ አድርግ። በኢየሱስ ስም። አሜን።

99 [አንዲት እህት በልሳን ተናገረች። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] የተናገረውን አናውቅም። አንድ ነገር ሊነግረን ፈልጎ ሊሆን ይችላል፣ ስለዚህ ለአፍታ ብቻ በትህትና ጠብቁ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። አንድ ወንድም ትርጓሜ ሰጠ።]

100 አሜን። ጠላት በመጣ ጊዜ... ? [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ከቅዱስ ቃል እንብባችሁ ታውቃላችሁ፡ ጠላት ኃይሉን እጅግ ስላበረታባቸው፡ ሁሉም... አንድ ሆነው በነበሩ ጊዜ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በአንድ ሰው ላይ ወረደና፡ የት ሄደው፡ መጠበቅ እናዳለባቸው፡ በትንቢት ተናገረ፡ ጠላታቸውንም አጠፉት። እነሆ አሁንም መጥቷል። እያችሁ፡ ጠላታችሁ የምታጠፉበት ቦታ አለ፡ የእግዚአብሔርን እጅ ያዙ። የእግዚአብሔር እጅ ክርስቶስ ነው፡ ይህም፡ ቃሉ ነው፡ ስለዚህ ዛሬ ማታ የጸሎት ሰልፍ ስንጠራችሁ ይህ በልባችሁ ይኑር።

101 ቢሊ ዛሬ እንደገና የጸሎት ካርዶችን እንዳከፋፈለ አምናለሁ። ቢ፣ ቢ፣ እስኪ ቢ ሰማንያ-አምስትን፡ እንውሰድ። ትናንት ማታ፡ አስራ አምስት ያህል አስተናግደናል። ብዙ ጊዜ በየምሽቱ አሥራ አምስት ያህል ለማስተናገድ እንሞክራለን። ካርዶቻችሁን ያዙ፡ እንቀበላችኋለን፡ አሁን። አስራ አምስቱን እንሞክር። ሰማንያ-አምስት። ቢ፡ ማለት፡ እንደ ብራንሃም። ቢ፡ ሰማንያ-አምስት እስከ መቶ። ቢ፡ ሰማንያ-አምስት የያዘ ማነው፡ እስኪ... እጅህን ወደላይ አንሳውና፡ እንየው። ልክ ነው ግን... እሺ፡ በጣም ጥሩ፡ ከኋላ አለ፡ ሰማንያ-አምስት ወደዚህ ና።

102 እንዴት እንደሚደረግ፡ የማያውቁ እንግዶች ሊኖሩ ስለሚችሉ... ልጄ ይመጣል። ልጄ ወይም ሌላ ሰው፡ ይመጣል፡ ካልቻለ፡ ወንድም ቦርደርስ፡ ወይም ሌሎች ይመጣሉ። አንድ ሰው ወደዚህ ይመጣና፡ ከእነዚህ፡ አንድ መቶ ካርዶችን ይወስዳል፡ በሕዝቡ ፊት ይቆማል ሁሉንም ያቀላቅላቸዋል። ከዛ በኋላ ካርዶቹን ያከፋፍላችኋል፡ ወደ መድረክ ትጠራላችሁ አይላችሁም፡ ያንን አያውቀውም። እኔም አላውቅም። ማታ መጥቼ፡ ከካርዶቹ መካከል፡ አስር ወይም አስራ አምስት ያህል፡ መዝዤ አወጣለሁ። ያ ግን ከፈውሳችሁ ጋር በምንም አይገናኝም። እዛ ቁጭ ማለት ትችላለህ። የትላንቱ ማታ፡ አስታውሱት። እስኪ ትላንትና ማታ፡ እዚህ የነበራችሁ እጆቻችሁን አሳዩን? ሰዎች እንዲሁ በጉባኤው ላይ ፈውሳቸው እንዴት እንደተቀበሉ!

103 አሁን፡ ሰማንያ-አምስት፣ ሰማንያ-ስድስት፣ ሰማንያ-ሰባት፣ ሰማንያ-ስምንት፣ ሰማንያ-ዘጠኝ፣ ዘጠና። ቢ፡ ሰማንያ-አምስት፣ ሰማንያ-ስድስት፣ ሰማንያ-ሰባት፣ ሰማንያ-ስምንት፣ ሰማንያ-ዘጠኝ፣ እስከ ዘጠና፣ አሁን ወደዚህ ይምጡ። አንዱ ይህ ነው... አዎን፡ የሚያስፈልገን... ምናልባት ሌላ ሰው... አዎን፡ አንደኛውም እዚህ አለ፡ በቃ ጥሩ ነው። ዘጠና፣ አሁን ከዘጠና እስከ መቶ። ዘጠና፣ ዘጠና-አንድ፣ ዘጠና-ሁለት፣ ዘጠና-ሶስት፣ ዘጠና-አራት፣ ዘጠና-አምስት፣ ዘጠና-ስድስት፣ ዘጠና-ሰባት፣ ዘጠና-ስምንት፣ -ዘጠኝ።

104 መንቀሳቀስ የማትችሉ፡ ከሆናችሁ... አሁን እዚህ፡ ሁለት ሶስት ዊልቸሮች፡ ይታዩኛል፡ አራት ያየሁ፡ ይመስለኛል። የጸሎት ካርድ አግኝታችሁ፡ ቁጥራችሁ—ተጠርቶ፡ መንቀሳቀስ የማትችሉ ከሆናችሁ፡ እጃችሁን አሳዩን፡ ወደዚህ እንድትመጡ እንረዳችኋለን።

105 የጸሎት ካርድ ከሌላችሁ ግን ባላችሁበት ሆናችሁ ጸልዩ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ዛሬ ማታ—ይሁንልኝ—የእኔ ትሁን፡" በሉት። የጸሎት ካርድ ያልደረሳችሁ ካላችሁ፡ እጃችሁን አሳዩን። ኦ፡ ማይ! እስኪ እንዲህ እንበል፡ በሌላ እንዳትረዱኝ ተሰፋ አደርጋለሁ። አንድ ጊዜ ግን፡ የጸሎት ካርድ ያልነበራት ሴት ነበረች እንበል። ሴቲቱ በብዙ ግፊያ መካከል ገብታ፡ እንዲህ አሰበች (አሁን በደንብ አድምጡኝ)፡ "የዚህ ሰው ልብሰ ጫፍ ብነካ፡ እፈወሳለሁ" ብላ አሰበች። ታሪኩን ሰንቶች ታዉቁታላችሁ? መልካም። ምን አደረገች? ነክታው ሄደችና፡ ቁጭ አለች። ኢየሱስም ዞር አለ፡ የት እንደነበረች ያውቃል። አይደለም'ዴ? ችግሯን ያውቀዋል። አይደልም'ዴ? ችግሯን ስለሚያውቅ፣ ችግሯ ምን እንደነበረ ነገራት። በውስጥ ሰውነትዋም የደም ችግሯ መድረቁን ተሰማት። አይደለም'ዴ? ለምን? ስለነካችው ነው።

106 እስኪ፡ እንደ እብራውያን፡ እንደ እብራውያን መጽሐፍ መሰረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የድካማችን ሰሜት የሚነካው ካህን፡ ሊቀ ካህን እንደሆነ ሰንቶች ታውቃላችሁ? ነው? በጣም ጥሩ፡ እንግዲያውስ ያው መዓርግ የያዘ፡ ያው ሊቀካህን፡ ሊቀ ካህን ከሆነ፡ ምን ምን ያደርጋል ትላላችሁ? ያኔ ያደረገው አሁንም ያደርገዋል። ይህን ታምናላችሁ? ብታምኑት፡ ያኔ ያደረገው አሁንም ያደርገዋል። በጣም ጥሩ። ሰንቶች ታምኑታላችሁ፡ እጃችሁን ወደ ላይ አርጉና፡ "እኔ በርግጥ አምናለሁን"? በሉ

107 እሺ፡ የጸሎት መሰመር ከመሰራታቸው በፊት፣ እዚያ የጸሎት መሰመር እናድርግ። እሱ እዚህ እንዳለ አውቄአለሁና። ህ—ህ—ህልውናው ይሰማኛል፡ እዚህ—መሆኑን አውቄአለሁ። ኑ። የጸሎት መሰመር ዝግጁ ነው? ወደዚያ ልጥራ ብዬ ነበር። ዝም ብላችሁ—ጸልዩ፡ ወደዚህ አቅጣጫ እያያችሁ፡ አምናችሁ ጸልዩ።

108 እዚህጋ ወደ እኔ እያየች የተቀመጠችው ሴት፡ መነፅር ካደረገች ሴት አጠገብ ተቀምጣ ታየኛለች። ሴቲቱ በላይዋ ላይ የሚንሳፈፈው ነገር አይታያችሁምን? ወደዚህ ተመልከቺ። አያችሁ? በልብ ህመም እየተሰቃየች ናት። እግዚአብሔር እንደሚፈውሰሽ ታምኛለሽ? ካመንሽ እጅሽን አንሺ። ችግርሽ ያ ነበረ። አዎን። አሁን ችግርሽ ያ ከነበረ፡ ህዝቡ እንዲያይሽ፡ እጅሽን **እንዲህ** አድርጊውና ወደ ላይ አንሺው። አሁን፡ ከአሁን በኋላ ከአንቺ ተነሰቷል። እምነትሽ አድኖሻል።

109 ትናንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው። ኦህ፡ ባላንጣው ቢኖርም'ኳ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው። ነው... ልብ በሉ፡ ጸልዩ ብቻ፡ ታውቁት ዘንድ፡ ወደዚህ መጠራት አያስፈልጋችሁም።

110 ይህችም፡ አንድ እመቤት ናት። እስከማውቀው ድረሰ በህይወቴ ሁሉ አይቻት አላውቅም፡ ትጠራ አትጠራ ሳላውቅ፡ ወይም የጸሎት ካርድ ይኑራት አይኑራት ሳላውቅ፡ እዚህ የቆመች ሴት ናት። ሰው የጸሎት ካርድ ሰጠሸ፡ ከዛም ቁጥ—ቁጥርሽ ተጠራ፡ ወደዚህም መጣሽ። እውነት ነው? ምን እንደሆንሽ፣

ማን እንደሆንሽ፣ ከየት እንደመጣሽ፣ ምን እንደፈለግሽ፣ የማውቀው ነገር የለም። እኔ ሌላ ሰው ነኝ፡ አንቺም ሌላ ሴት ነሽ። አዎን። እንዲህ አይነት አጋጣሚ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ በዮሃንስ ወንጌል 4ተኛ ምዕራፍ ላይ ሆኗል።

111 ምናልባት “ወንድም ብራንሃም፡ ቅድም፡ እንዴት አድርገህ፡ ይህን አደረግከው፡” ልትሉ ትችላላችሁ? ማርሽ ጥርሱን ብቻ ጎትቱት፡ አያችሁ። እኔ አላውቅም፡ አያችሁ። ይሄን ማድረግ የሚችለው እሱ ራሱ ነው። እኔ አላውቅም። የሴቲቱ ጉዳይስ እንዴት ሆነ? በህይወቴ ያቺን ሴት አይቻት አላውቅም። ለእኔ ፍጹም እንግዳ ናት። አምናለሁ ሴት ናት። አሁን በጉባኤው መኻል የተፈወሰው ሰው አለ ማን ነው? ፍፈቃደኛ ከሆንሽ... አዎን። ሁለታችንም አንተዋወቅም። እውነት ከሆነ፡ እጅሽን **እንዲህ** አወዛውዢው። አያችሁ? ሴትዮዋን አይቻት አላውቅም። እሷ ግን እምና ተቀምጣ ነበር። አሁን፣ የሆነ ነገር ነካች፣ አይደል? እኔን መንካቱ ምንም አይጠቅምም።

112 አሁንስ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አታዩምን? ትናንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነናል እርሱም ክርስቶስ ነው። አያችሁ? ትክክለኛው ዘር እሱ ነው። እውነተኛው መንፈስ ቅዱስ ወደ ትክክለኛው የቃሉ ዘር ውስጥ፡ ከገባ... በከፊል ብቻ አይጠቀምም (ምክንያቱ፡ ዲያብሎስም እንዲሁ ያደርጋልና)፡ አያችሁ፡ ቃል ሁሉ፡ በሙላት መጠቀም አለባችሁ፡ እሱ አምላክ ነውና፡ ግማሽ አምላክ አይደለምና። አያችሁ? የሆነውም ይህ ነበር።

113 አሁንም፡ ይህች ሴት ደግሞ፡ አይቻት አላውቅም። ኢየሱስ እንደዚህ አይነት ሴት አንድ ጊዜ አገኘ፡ ምናልባት ተመሳሳይ ሁኔታ ላይሆን ይችላል፡ አላውቅም። ወደ ሰማርያ መውረድ ስለፈለገ። ሰማርያም ከኮረብታው በታች እንደነበረች፡ እናውቃለን። በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጧል። ወደ—ኢያሪኮ መንገድ ላይ ነበረ፡ ማለቴ ነው፡ እና በሰማርያም ማለፍ ነበረበትና፡ ሲካር ወደምትባል ከተማ መጣ። በጉድጓዱም አጠገብ ተቀመጠ፡ ደቀ መዛሙርቱን ምግብ ሊገዙ ልኳቸው ነበርና።

114 በአለም ውስጥ ስንት የሰዎች ዘር ሐረግ አሉ? ሦስት። የካም፣ የሴም፣ እና የያፌት ሰዎች። ሁላችንም ከኖህ የመጣን ነን። የቀረውም ዓለም በዚያን ጊዜ ወድሟል። ሦስት የሰዎች ዘር ሐረግ ብቻ አለ፡ አይሁድ፣ አህዛብ እና (ግማሽ አይሁዳዊ እና ግማሽ አህዛብ) የነበሩ ሳምራዊያን። አሁንም በዓለም ውስጥ ያሉት የዘር ሐረጎች፡ አያችሁ፡ እነዚህ ሦስቱ ብቻ ናቸው።

115 በእግዚአብሔር ዘንድ ነገር ሁሉ በሦስት ፍጹም ይሆናል። ልክ ዛሬ ማታ ስለ ሦስቱ እያወራሁ እንደነበረ ነው፤ ሶስት የባላንጣነት ደረጃዎች፡ ሶስት ቃል በስጋ የተገለጠባቸው ደረጃዎች፡ እያለ ይቀጥላል። አያችሁ?

116 እዚህጋ፡ ከአይሁዶች ጋር—ሲነጋገር፡ ፊልጶስ ናትናኤልን፡ ይዞ በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለው፡ “ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ፡” ሲለው፡ እሱ በዚያ ነበርና። እንድርያስም... ጴጥሮስን ባመጣ ጊዜ፡ “ስምህ ስምዖን ነህ፡ ከአሁን ጀምሮ ‘ጴጥሮስ፡’ ትባላለህ።” አንተ፡ “የዮና ልጅ ነህ።” አያችሁ? እነዚህ ሁሉ፡ አይሁዶች ነበሩ።

117 እዚህጋ ግን ወደ አሕዛብ ወረደ... ወደ አሕዛብ ሳይሆን፡ ወደ ሳምራውያን ወረደ።

118 የአህዛብ ዘመን አሁን ነውና። በአሕዛብ መካከል ይህን አንድም ጊዜ አድርጎት አያውቅም። በጭራሽ። ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሩ። ነገር ግን በሉቃስ 22 ላይ፣ ከመምጣቱ በፊት እንደሚያደርገው ቃል ገብቷል።

119 በዚያ ተቀምጦ ሳለ፡ ግማሽ አይሁዳዊትና ግማሽ አሕዛብ የሆነች አንዲት ሴት መጣች። እሱም "አንቺ ሴት፡ የሚጠጣ ውኃ አምጪልኝ፡" አላት።

120 እሷ ግን፦ "ይህን ከእኔ መጠየቅ፡ በጣም፡ አይገባህም። እኛና እናንተ... በመካከላቸው አለመተባበር አለና። አንተ አይሁዳዊ ነህ፡ እኔም—ሳምራዊት ነኝ።"

121 እርሱም፦ "ከማን ጋር እንደምትናገሪ ብታውቂ ግን፡ የሚጠጣ ትጠይቂኝ ነበርሽ አላት።" ምን እያደረገ ነው? መንፈሷ ጋር እየተገናኘ። የሚያስቸግራት ነገር ምን እንደሆነ ባወቀ ጊዜ፡ ሂጂና፡ ባልሽን ይዘሽ ነይ አላት። ባል የለኝም አለችው። እሱም "ልክ ነሽ፡ አምስት ባሎች ነበሩሽና፡" አላት።

122 አሁን፡ ተከታተሉኝ፡ ፈሪሳውያን ይንን ሲያደርግ አይተውታል። ልክ፡ ተቃራኒው ልክ በቃሉ ዙርያ ነበር፡ ምን አሉት? "ይህ ሰው ብዔል ዜቡል ነው፡ ሟርተኛ ነው፡" አሉት። አያችሁ?

123 "መንፈስ ቅዱስ ይህንኑ ለማድረግ ሲመጣ፡ በሱ ላይ የሚናገር ሁሉ ይቅር አይባልለትም፡" ብሏል ኢየሱስ። ይኸው ተቃራኒያችሁ አለላችሁ። አያችሁ? ያኔ ግን ይቅር እንደሚላቸው ተናገረ፡ መንፈስ ቅዱስ አልወረደም ነበርና፡ በጉ፡ የመስዋዕቱ በግ አልሞተምና።

124 ሴትየዋ ግን እንደዚያ አላሰበችም። "ጌታ ሆይ፡ አንተ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ፡" አለችው። ለብዙ መቶ ዓመታት በመካከላቸው ነቢይ አልነበረም። እሷም፦ "ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ። ክርስቶስ የተባለው፡ መሲሕ፡ እሱ ሲመጣ፡ እንዲህ እንደሚያደርግ እናውቃለን፡" አለችው።

125 ያኔ፡ እንዲህ ካደረገ፡ እንግዲያውስ እሱ ትናንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው። ያኔ እራሱን የገለጠው በዚያ መንገድ ከሆነ፡ ዛሬም ያው አይሆንምን? መሆን አለበት! ስለዚህ አሁንም፡ ዛሬ አንድ ሴት እና አንድ ሰው ተገናኝተናል። እሷ ያቺ ሴት አይደለችም፡ እኔም ያ ሰው አይደለሁም። ያንኑ መንፈስ ቅዱስ ግን አሁን አለ፡ እርሱም ያደረጋቸውን ሰራዎች፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ዘመን እኛም እነዚህን እንደምንሰራቸው ቃል ገብቷል።

126 እንግዲህ፡ እኔ አላውቅሽም (አንቺም እውነት እንደሆነ ታውቂያለሽ)፡ በጭራሽ አንተዋወቅም፡ አንቺም እዚህ ቆመሻል። ምናልባት... የገጠመሽ ነገር ሊኖር ይችላል፡ ላይኖርም ይችላል፡ እኔ አላውቅም። ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱሱ፡ ችግርሽን ቢገልጥልኝ ግን፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ እንጂ፡ ሰው እንዳልሆነ ታምኚአለሽን? ይህ ድንኳን ብቻ ነው፡ **ይህ** እግዚአብሄር ሊሰራበት የመረጠው፡ የሚሰራበት ማደርያ ነው። ያንን የሚያደርገው—በሉዓላዊ ጸጋ እና በምርጫ ነው። ስለዚህ፡ አምነሻል። ታምኛለሽ? [ያቺ እህት "ኣሜን፡" አለች።—እርታዒ።]

127 በጉባኤውስ ስንቶች ታምኑታላችሁ? በህይወት ተገናኝተን የማናውቀውን ሁለታችንም፡ በዚህ በብርሃን ፊት ቆመናል፡ ሴቲቱ ማን እንደ ሆነች፣ ምን እንደ ሆነች፣ ከየት እንደመጣች፣ ምን እንደምትፈልግ አላውቅም። ሴቲቱን በህይወቴ

ውስጥ **እዚያ ላይ** አይቻት እንደማላውቅ ሁሉ፡ ይህችም በህይወቴ አይቻት አላውቅም፣ ነገር ግን፡ አንድ ነገር እንድታደርጉ እፈልጋችኋለሁ፡ እያችሁ፡ ያንን ባላንጣ ከመካከላችሁ አሁን አርቁት፡ ቃል ተገልጦ በመካከላችን ስጋ ሲለብስ አይታችሁ እመኑ። ቃሉ በገዛ ሥጋችን ሕያው ሆኗል፡ ይህም የእግዚአብሔርን ህልውና ያሳያል።

128 የልቧን ሐሳብ ይሰጣት አሁን። ፍለጋዋ በቂ ምክንያት አለውና። ልጅ የላትምና፡ ልጅ ትፈልጋለችና። ዕድሜዋ አርባ ዓመት ገደማ ነው። በእርግጠኝነት የማይቻል ዕድሜ አይደለም።

129 በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ መካን ሆነው የነበሩ ሴቶች፣ አሁን በጉባኤው ውስጥ አሉ፡ ወደ መሰውያው እንዳቺ መጥተው፡ ጌታ ልጆች አሰታቅፏቸዋል። ይህን የምታውቁ ሰዎች እጃችሁን ከፍ አድርጉ። አየሽ? አየሽ? በቀደም ለት፡ እሁድ ከሰዓት፡ ከዚህ ከወጣሁ በኋላ፡ ቆንጆ ሴት ልጅ ተወልዳ አቅፌአለሁ፡ እናቷ መካን ነበረች፡ ጌታ ግን ተናገራት። ህጻኗ ልጅ፡ ጣፋጯ ትንሽ ነገር፡ ዛሬ እዚህ አለች? የት ናት? አዎን። ያቻትና፡ እዚያ ማዶ፡ ቁጭ ብላለች። እናቷ ቁጭ ብላለች። ህጻኗ፡ ራሷም ያቻትና። ተመልከቻት? ከእግዚአብሔር ዘንድ የተነገረች ቃል ነበረች።

130 አሁንስ፡ በሙሉ ልብሽ ታምኚዋለሽ? አሁን በተቀበልሽው በረከት ታምኚያለሽ፣ በውስጥሽ ያለው በረከት፡ የእግዚኣብሄር መልስ እንደሆነ ታምኚአለሽ? እግዚአብሄር ሰምሽን ማን እንደ ምትባይ ከገለጠልኝ፡ ለልጅሽ ሰም ትሰይሚያለሽ፡ ታምኚያለሽ? ስለዚህ፡ አንቺ ወይዘሮ ቶምፕሰን በሙሉ ልብሽ ካመንሽ፡ ወደ ቤትሽ ሂጂ፡ ልጅም ተቀበይ።

131 በሙሉ ልብህ አምነሃል? እመን ብቻ፡ አትጠራጠር፡ እግዚአብሔርን እመነው። እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው።

132 እንዴት ነህ፡ ጌታዬ? ከአንተ ጋርም፡ የምንተዋወቅ አይመስለኝም። አንተን በህይወቴ እንዳየሁህ፡ ያወቅኩበት ብቸኛው ጊዜ፡ አሁን ወደዚህ ስትመጣ ብቻ ነው። ስትመጣ ሳይህ፡ የወንድም ሻካሪያን፡ ማለቴ ማነው... ስትመጣ የዘማሪው ማሻጊያን፣ የወንድም ማሻጊያን አጎት መሰለኸኝ ነበር። ከዛም ወደ ስልፉ ስትገባ አየሁህ። ስለዚህ አሁን፡ ሰለማንተዋወቅ፡ ወይም፡ እኔም አንተም፡ ሁለታችንም፡ እንግዳ ሆነን ሳለን። አሁን፡ ጌታ ኢየሱስ የአንተ ነገር ከነገረኝ—ምናልባትም፡ አንተ የምትፈልገውን ካሳወቀኝ፡ ማለት፡ አንተ፡ የምትፈልገው ነገር ነገረኝ እንበል። ይህ ማለት፡ ቀድሞ አድርጎልሃል ነው። ለማመን የበቃ እምነት ብቻ ይኑርህ።

133 አሁንስ፡ ሰንቶች ይሄን ትረዳላችሁ? የለመናችሁትን እንዳገኛችሁ በቂ እምነት ብቻ ይኑራችሁ! እያችሁ?

134 አሁን፡ አሁን፡ የሆነ ነገር ፈልጋችሁ እዚህ ከሆናችሁ፡ እና ፍላጎታችሁ ምን እንደሆነ እኔ ሳላውቀው፡ እርሱ ግን ጸሎታችሁን ከነገረኝ፡ ይህ የሚያደርግ ሌላ ኃይል አለ ማለት ነው። አሁን፡ እንደ ቃሉ፡ ያንን ለማድረግ ቃል ገብቷል። በልባቸው ውስጥ ያለውን ሐሳብ ያውቃል። ልክ ነው? በጣም ጥሩ።

135 ለመፈወስ ትልቅ ፍላጎት አለህ። አንደኛው፡ በከባድ የነርቭ ችግር፡ በነርቭ ህመም እየተሰቃየህ ትገኛለህ። እውነት ነው። ሌላም፡ የጀርባ ህመም አለብህ፡ ጀርባህ ለተወሰነ ጊዜ በጣም አሰቃይቶሀል፡ ቀዶ ጥገናም አድርገህ ነበር።

የሰርዊት ጌታ እግዚ አብሔር እንዲህ ይላልና። እውነት ነው። አየህ። ትክክል ነው። ሌላ የውስጥ ፍላጎትህ፡ ይህ ነው፡ በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ፡ ትልቅ መሻት አለህ። ትክክል ነው። ና ወደዚህ።

136 አምላክ ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ ይህ ሰው ከዚህ ሳይወጣ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላ፡ በኢየሱስ ስም። አሜን።

ተቀበል ወንድሜ። እምነት ብቻ ይኑርህ፡ አትጠራጠር።

137 እንደምን አለሽ? እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ እንደማንተዋወቅ፡ እገምታለሁ። ያ ትክክል ከሆነ፡ ሰዎች፡ እንደማንተዋወቅ እንዲያውቁ፡ እንግዳ መሆናችንን እንዲያዩ ብቻ እጅሽን አንሺ። እኔ እስከማውቀው፡ በህይወቴ አይቻት አላውቅም። ጉባኤው ውስጥ ካልሆነ በቀር፡ አይታኝ አታውቅም ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም እስከማውቀው፡ በህይወቴ ሴቲቱን አይቻት እንደማላውቅ፡ የሰማይ አባት ያውቃል፡ ቃሉም፡ ከፊቴ ተቀምጧልና። እንዲህ ከሆነ፡ ለምን እንደመጣሽ አላውቅም፡ ማን እንደሆንሽ፡ ምን እንደ ሆንሽም፡ ስላንቺ የማውቀው ነገር የለም። ልነግርሽ የምችለው ነገር የለኝም።

138 አንድ የማውቀው ነገር፡ ጸጋ መሆኑን ብቻ ነው። ቅድም ሰናገር… ከሰማሽኝ። እወስዳለሁ፡ የሚለኝን እሰማለሁ፡ የማየውን፡ እናገራሁ። ያላለውን፡ ማለት አልችልም። ከራሴ ብናገር፡ ስሕተት ይሆናል። አየሽ? ስህተት ይሆናል። እሱ ከተናገረ ግን፡ ፍጹም ትክክል ነው። በጭራሽ፡ ተሳስቶ አያውቅም። አምላክ እስከሆነ ድረስ ፈጽሞ አይሳሳትም። አያችሁ? አያችሁ፡ እግዚአብሔር አይሳሳትምና።

139 ነገር ግን እግዚአብሔር የምትፈልጊውን፡ ፍላጎትሽን ቢነግረኝ፡ ወይም—ለምን እንደመጣሽ፡ ያደረገሽው ነገር፣ ወይም ሌላ፡ መሰል ነገሮች ቢነግረኝ፡ ወይም ማን እንደ ሆንሽ፡ ከየት እንደመጣሽ፡ እሱ ሊነግረኝ የሚፈልገውን ሁሉ፡ ቢገልጽልኝ ታምኛለሽ? አመሰግናለሁ።

140 አንዱ ነገር፡ እግርሽ ላይ ችግር አለ። እግርሽ ያስቸገርሻል። ትክክል። ከፍ አርጊ… የሴቶች ችግር፡ የሴት ጉዳይ መዛባት አለብሽ። በልብሽም ታላቅ መሻት አለ፡ የሆነ ሰው ወይም የሆነ ነገር ጠፍቶብሻል። ወንድ ልጅሽ ነው፡ ልጅሽ ከቤት ወጥቶ፡ ጠፍቶአል፡ ወደ ቤት ተመልሶ እንዲመጣም እንድጸልይ ትፈልጊኛለሽ።

141 የሰማይ አምላክ ሆይ፡ ልጇን ዛሬ መልስላት። መንፈስ ቅዱስ ያንን ወጣት ዛሬ ማታ ከመንገድ ያቁመው፡ ወደ እናቱ ይመልሰው። በኢየሱስ ስም። ኣሜን።

142 ሁሉን የሚያውቅ እርሱ መልሶ ያመጣልሻል። አትጨነቂ። አሁን እመኚ፡ አትጠራጠሪ። በሙሉ ልብሽ እምነት ይኑርሽ። አንቺ እመኚ፡ ሌላው ሁሉ እግዚአብሄር ያደርገዋል።

143 እነዚህ ያደረግኳቸው ሶስት ወይም አራት የመለየት ጸጋዎች፡ ሌላም ይሁን እንጃ፡ አያችሁ፡ ማየት—እስከማልችል ድረስ አድርሶኛል። ልገልጸው አልችልም፡ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። ምናልባት “ቆመክ ከሰበክባቸው አርባ-አምስት ደቂቃዎች ይከፋል ማለትህ ነው፡” ትሉኝ ይሆናል? አዎን፡ ጌታዬ። ሶስት ሰዓት ቢሆንም፡ አይተካከለውም።

144 አንዲት ሴት ጌታችን ኢየሱስን ልብሱን ነካች። በርግጥ እነዚህ ሰዎች አልነኩኝም። ነገር ግን፡ እቺ ሴት፡ ወደዚህ ተመልከቱ፡ እንዲህ ታደርጋለች…

(እጅሽን በእኔ ላይ አድርጊው። አያችሁ? ) እኔን ነክታኛለች፡ ሰው ነኝ፡ ምንም አልሰራላትም። እሱን እንድትነካ ያስፈልጋታል። እኔም፡ በቃ—በቃ፡ በጸጋው ብቻ... እወስዳለሁ፡ ሁለመናዬ ይወስዳል፡ የማየውንም ሁሉ እናገራለሁ። አያችሁ? ይኸው ነው። አያችሁ፡ እኔን መዳሰስ ትርጉም የለውም፡ እሷ ግን በእኔ አልፋ ኢየሱስን ዳሰሰች። ያቺ ሴት በኢየሱስ አልፋ እግዚአብሔርን የዳሰሰችው በዚህ መንገድ ነበር፡ እሱ ግን ችግሯ ምን እንደነበረ አላወቀም ነበር። ልብሱን ብቻ ነካችና፡ ሄዳ ተቀመጠች። እርሱም—እርሱም "የነካኝ ማን ነው? " አላቸው፤

145 ሐዋርያትም አሉት፦ "እንዴ፡ ለምን እንዲህ ትላለህ፡ ሰው ሁሉ እየነካህ አይደል? "

"ኃይል ከእኔ ወጥቷል፡" አላቸው።

146 እንግዲህ፡ ኃይል ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? ጉልበት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ፡ አንድ ሴት ስለነካችው ብቻ ደከመ። በጸጋው ብቻ የዳንኩ፡ እኔ፡ ሐጢአተኛውስ? ለምን እንደሚበረታብኝ ታውቃላችሁ? "እኔ የማደርገውን፡ እናንተም ታደርጋላችሁ። እኔ ወደ አብ ስለምሄድ፡ ከዚህም የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡" ብሎ ስለተናገረ ነው። "የሚበልጥ፡" የሚለውን ቃል በትክክለኛ የግሪክ ቋንቋ፡ "ከዚ በላይ ታደርጋላችሁ" የሚል ትርጉም ይዞአል።

147 አሁን፡ ሴቲቱን አላውቃትም። ስለሷ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም። እሷ ለእኔ እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ለእኔ እንግዳ ነች። አንዳችን ለሌላው እንግዳ ነን። ምናልባትም ሰዎች እንዲያውቁ፡ እጅሽን ከፍ አድርገሽ፡ "አንተዋወቅም፡" በያቸው። አሁን፡ የእግዚአብሄር ልጅ፡ በእንዲህ አይነት ትዕይን፡ በጉድጓዱ አጠገብ አንድ ቀን ሴት አግኝቶ ሲያናግራት፡ ጥቂት አነጋገራትና፡ ችግሯ ምን እንደሆነ አወቀ፡ ችግሯ ምን እንደሆነ ነገራት። ስለዚህ መሲሑ እንደ ሆነ፡ በዚህ አወቀችው። አሁን አንቺ—አንቺ እኔን... ነክተሽኛል፡ እኔም ነክቼሻለሁ፡ ምንም አልተፈጠረም። ነገር ግን የእኔ እምነት (በስጦታ) እና በአንቺ እምነት (በስጦታው በማመንሽ) እሱን ሊነኩት ከቻሉ፣ በእኔም አልፎ... በኔ በኩል ከተናገረሽ፡ እንግዲያውስ ያኔ በሲካር ጉድጓድ አጠገብ እንደነበረ—አሁንም እዚህ እንዳለ እወቂ። አየሽ? ትናንትናና፣ ዛሬም እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው። ታምኛለሽ?

148 ብዙ ችግሮች፡ ብዙ ደዌ፡ የተወሳሰቡ ነገሮች አሉብሽ! እንዲጸለይልሽ ከምትፈልጊአቸው ዋና ዋና ነገሮች አንዱ አርትራይተስ ነው። ትክክል ነው። ልክ ነው? በአርትራይተስ የተነሳ እየደረቅሽ ነሽ። እጅሽን ከፍ አርጊው...

149 በደንብ ካስታወስኩት፡ ስትራመጂ በቀስታ ነው። ቆይ አንዴ ትንሽ ደቂቃ ጠብቂ፡ ምናልባት ይሄን ነገር የሚጋፋ ሌላ ንግግር እንዳይኖር... ማለት፡ ታውቃላችሁ፡ አንድ ነገር ይሰማችኋል፡ ሰዎችም፡ እንደምታውቁት፡ ተቃውሞን ይተነፍሱበታል። ሌሎች "ኧረ፡ ግምት ነው፡" ወይም፡ እንዲህ የመሳሰሉ፡ ነገሮች፡ ይናገራሉና።

150 አንቺ ግን፡ ጥሩ ሰው ትመስያለሽ፡ እስኪ ጥቂት ላውራሽ። እዚህ ጥቂት ቆም እንበል፡ ምክንያቱም በልብሽ ውስጥ ከእግዚአብሔር የምትፈልጊው ሌላ ነገር እንዳለ አስቤአለሁና። እንግዲህ፡ እኔ የጸሎትሽ መልስ መስጠት አልችልም፡ እሱ ግን ይችላል-... ምክንያቱ፡ ካመንሽ፡ አስቀድሞ መልስ ተስጥቶታል።

ማመን ከፈለግሽ፡ እንድታምኚ ለማድረግ። አሁን፡ በጣም ስለምትወጂው ሰው ጉዳይ፡ እነግርሻለሁ፡ እዚ የለም፡ ወንድምሽ ነው። ወንድሽ እዚ አገር የለም። ብዙ ሐይቆች ባሉበት፡ መኖርያው ውኆች ባሉበት አገር ነው። እንደ ሚቺጋን ዓይነት ብልሽሰ... አዎን፡ የሚገኘው ሚቺጋን ነው። እናም ገዳይ በሆነው፡ በማይድነው በኩላሊት በሽታ እየተሰቃየ ይገኛል። አዎን፡ አይደለም'ዴ? የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። አሁን፡ ወደ እግዚአብሔር ያነሳሽውን፡ በእጅሽ ያለውን መሀረብ፡ ለወንድምሽ ላኪለት፡ እንዲያምን እንጂ፡ እንዳይጠራጠር ንገሪው፡ ያ ነው፡ አንቺ ካመንሽ አሁን ይፈወሳል።

151 በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? አየሽ፡ አሁን፡ ካመንሽ፡ ከአንቺ የሚጠበቀው ነገር ቢኖር፡ ይህ ነው፡ በፍጹም ልብሽ ተቀበይው። ልክ ነው?

152 እሺ አሁንም፡ "ሰዎችን፡ እያያቸው ነው። ሰለሚያያቸው ነው፡ እንዲህ የሚያደርገው ልትሉኝ ትችላላችሁ።" እንግዲህ ከባድ ነው!

153 ይሄን ግን ላታውቁት ትችላላችሁ... ይህች የታመመችው፡ እመቤት፡ ማንም ትሁን፡ ነይ ወደዚህ፡ እመቤት፡ እዚህጋ ሁኚ። አሁን እያየኋት አይደለሁም። እግዚአብሔር ችግርሽን ሊገልጽልኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? ካመንሽ፡ እጆችሽን አንሺ፡ ያቺ እመቤት፣ ያቺኛዋ እመቤት፡ የታመመችው። አዎን። አዎን። እሺ፡ እንግዲህ በሙሉ ልብሽ ካመንሽ፡ የአዝማ በሽታ ከእንግዲህ ወዲህ አያሰጨንቅሽም። እሺ፡ እመኚና ቤትሽ ሂጂ!... ? ...

154 እሷን አላየኋትም፡ አይደል? አየሽ፡ ወዲህ... አንቺም **ወዲያ** እያየሽ፡ ምንም ቢሆንም ራዕዩ ይሆናል። አሜን! አይታያችሁም? እግዚአብሔር ፍጹም እንደሆነ ሁሉ ይህም ፍጹም ነው!

155 አንተስ፡ ታምናለህ? አንተም፡ አዝማ ሊተውህ እንደሚችል፡ አይችልም'ዴ? እንደሚችል ታምናለህ? በጣም ጥሩ፡ ሂድና ጌታ ኢየሱስን—እንደምታምነው ንገረው።

156 ይህ አርቲራይተሰ ሸባ ካደረገህ—አንድ ቀን ምርኩዝ ልታነሳ ትችል ነበርክ፡ ይሁን እንጂ አያደርግብህም። አትቀበለውም፡ አትቀበለውም አይደል፡ ትቀበለዋለህ'ዴ? ደህና እንደምትሆን ታምናለህ? ኢየሱስ ክርስቶስ አድኖሃልና፡ መንገድህ ሂድ።

157 የልብ ችግር ሰዎችን ይገድላል፡ አንቺን ግን አይገድልሽም። እግዚአብሔር እንደሚፈውሰሽ እና ደህና እንደሚያደርግሽ ታምኛለሽ? በፍጹም ልብሽ አምነሽ፡ "በእውነት አምናለሁ፡" እያልሽ ሂጂ።

158 እንግሊዘኛ ትናገሪአለሽ? እንግሊዝኛ ትችያለሽ? (አንድ ሰው ይምጣ።) እሺ፡ በጣም ጥሩ። ያልኳትን ሁሉ ትነግራታለህ? እንዲህ በላት፡ ካመነች የሆድ ችግር ይተዋታል ብለህ ንገራት። ታም—ናለች? የጀርባ ህመም፡ ይተውሻል፡ አሁን መንገድሽ በደህና መሄድ ትችያለሽ።

ጤና ይሰጥልኝ? ታምናለህ?

159 እኔ ይህ ሰናገር እኔን እያየኸኝ ያለኸው፡ የጀርባ ህመም ያመመህ፡ ከኋላ የተቀመጥከው አንተኛው። ሰር፡ አንተም፡ ከአመንክ፡ ልትፈወሰ ትችላለህ። እሺ፡ ሰር።

160 አጠገቡ የተቀመጥሽው እመቤት፡ የአንገት ችግር አለብሽ፡ አይደል፡ እመቤት? እግዚኣብሄር እንደሚፈውስሽ ታምኚአለሽ? ህጻኑ ልጅ ጉልበት ላይ እጅ እንዲጫንበት ትፈልጊያለሽ፡ እርሱም፡ ይፈወሳል። ታምኚያለሽ? የሴቶች ጉዳይ ያስቸግሻል፡ የእመቤቶች ችግር፡ ከእንግዲህ አይኖርም። እምነትሽ አድኖሻል ጤነኛም አድርጎሻል።

161 ኢየሱስ ክርስቶስን ትላንትም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘላለምም፣ ያው እንደሆነ ታምናለህ? እንግዲህ አንዳችን በሌላው ላይ እጃችንን ጭነን፡ የእምነት ጸሎት እንጸልይ፡ ሁላችንም የእምነት ጸሎት እንጸልይ።

162 አምላክ ሆይ፡ አሁን በመለኮታዊ ህልውናህ ተውጠን ሳለን፡ በየቦታው የታመሙትን እየፈወስክ፡ በጉባኤው ስታልፍ ማየት እንፈልጋለን። አምላክ ነህና። ጉባኤውን በሙሉ እንድትፈውሰው እጸልያለሁ። የእግዚአብሔር ፍሬሽ ትንፋሽ ወደ ልቦቻቸው ይዝነብ፡ ጊዜው እንዳለቀም ያሳስባቸው። ጥቂት ጊዜ ብቻ እንቆያለን፡ ከዚያ ግን ከምንወደው ጋር ለመሆን እንሄዳለንና። አሁንም ህልውናው ለሁሉ ፈውሰ ያምጣ።

163 ሰይጣንን እናወግዛለን፡ ድርጊቱን ሁሉ እናወግዛለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ አንተ ሰይጣን፡ ከሰዎች ሁሉ ውጣ።

164 አሁን እሱን ማመን የምትወዱ፡ እና ፈውሳችሁን የተቀበላችሁ ሁላችሁ፡ በእግሮቻችሁ ቁሙና፡ “አሁን አምኛለሁ፡ ፈውሴን ለመቀበል እቆማለሁ።” በሉ። ምንም ዓይነት ችግር ይኑራችሁ፡ በእውነት ካመናችሁ፡ በእግሮቻችሁ ቁሙ። አሁን እጃችሁን ወደ ላይ አንሰታችሁ፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ሰለፈወስከኝ፡ አመሰግንሃለሁ፡” በሉት። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን።

**የባላንጣው ዘር** AMH65-0118

(The Seed Of Discrepancy)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሰኞ ማታ፡ ጥር 18፡ 1965፡ ለሙሉ ወንጌል ቢዝነሰሰ ሜን ፌሎሺፕ ኢንተርናሽናል፡ በዩ.ኤ.ኤ. ፊኒክሰ፡ አሪዞና በሚገኘው የዌሰትዋርድሆ ሆቴል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org